TOURISM TRAINING INSTITUTE

# መስተንግዶ

## ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት

ቅጽ 55 ቁጥር 54 ሰኔ 2017 ዓ.ም






# የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት

## ተልዕኮ

የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን እድገት እና ልማት ለማፋጠን ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የክህሎት ስልጠና እና ትምህርት በመስጠት፤ የምርምር፣ የማማከር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎችን በማከናወን ሃገሪቱ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆን ማስቻል፡፡

## ራዕይ

በ2022ዓ.ም በቱሪዝም ዘርፍ በአፍሪካ ከሚገኙ አምስት የልህቀት ማዕከላት አንዱ መሆን፡፡

## ዕሴቶች

- እንግዳ ተቀባይነት/Hospitality
- አገልጋይነት/serving others
- ልህቀት/Professional  Excelence
- ጥራት/ Quality
- ፈጠራ/ Innovation
- የቡድን ሥራ/Team work

## የትኩረት መስኮች

- የላቀ የክህሎት ስልጠና፤
- የላቀ ምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር፤
- የላቀ ማማከርና የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት፤
- የላቀ ተቋማዊ አቅም።



# ማውጫ

## TABLE OF CONTENT


የክብርት ሚኒስትር መልዕክት 04

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር መልዕክት 06

የሥራ አመራርና አስተዳደር ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር መልዕክት 08

የቱሪዝም ማ. ኢንስ. የሥልጠናና ተቋማት አ. ግ. ዘርፍ ም/ዋና ዳ. መልዕክት 10

የኢንስቲትዩቱ የጥናት ምርምርና ማ. ዘርፍ ም/ዋና ዳ. መልዕክት 12

“ከልጅነት እስከ እውቀት በመምህርነት” ቆይታ ከመምህርት አንሰዩ ጋር 14

እንግዳ | ወ/ሮ ሳምራዊት ሞገስ 16

የጉዞ ማስታዎሻ 21

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ትናንት ዛሬ እና ነገ 26




መሪ ቃል (Motto)

**ለላቀ ብቃት እንተጋለን!**

*We strive for excellence!*


ዋና አዘጋጅ
አስቴር ተክሌ
አዘጋጆች
ዝናቧ ቱቾ እና ብሩክ ታደሰ



# የክብርት ሚኒስትር መልዕክት

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በሀገራዊ ልማት መሪ የልማት መሪ ዕቅድ ላይ የተመላከቱ ሀገራዊ ግቦች እንዲሳኩ የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተለይም መካከለኛና ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ባለሙያዎችን በሚፈለገው ዓይነትና መጠን አዘጋጅቶ ለሥራ ገበያው ለማቅረብ የሚያስችል ስትራቴጂ ከመንደፍ አንስቶ የሥልጠና ጥራትን እስከ ማረጋገጥ የዘለቁ ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

እነዚህ ሥራዎች በዘርፉ የሚያልፉ ዜጎች ተገቢውን እውቀትና ክህሎት እንዲጎናፀፉ፣ ሙያው በሚፈልገው ሥነ-ምግባር እንዲታነፁ፣ እና የሥራን ክቡርነት ተረድተው ለተግባር የተዘጋጁ እንዲሆኑ ማድረግን ያካትታሉ፡፡ ይህም የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ራዕይና ተልዕኮን ከሀገራዊ ራዕይና ተልዕኮ ጋር አሰናስኖ ለዕቅዱ ስኬት አስተዋፅኦ የሚበረክት ብቁና በቂ የሰው ኃይል ማፍራት ከዚህ ዘርፍ የሚጠበቅ እንደሆነ ለመረዳት ያስችላል፡፡

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና በሀገራችን አስተማማኝና ፈጣን የኢንዱስትሪ እድገት የሚያረጋግጥና በዓለም ገበያ የመወዳደር ብቃት ያላቸው ሙያተኞች የሚፈሩበትን እንዲሆን የሚያስችል አዲስ አሳቤ ቀርፆ ለተግባራዊነቱ ከፍተኛ ርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

አዲሱን የዘርፉን እሳቤ ተግባራዊነት ለማረጋገጥ በየደረጃው ከሚገኙ የዘርፉ ፈፃሚ፣ አስፈፃሚና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት በመስራት ዜጎች እንደየተሰጥኦና ዝንባሌቻቸው ክህሎታቸውን አዳብረው ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በርካታ ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው፡፡

ከእነዚህ ሥራዎች መካከልም ሙያና ሙያተኞችን

አስመልክቶ በህብረተሰቡ ዘንድ የተሻለ አመለካከት እንዲዳብር ለማስቻል እየተሰሩ የሚገኙ የገፅታ ግንባታ ሥራዎች በዋንኛነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር በሥራና ክህሎት ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት የሚኖረው አበርክቶ ከፍተኛ እንደሆነ እናምናለን፡፡

በውድድሮቹ የተካተቱ መርሃግብሮች ሙያና ሙያተኞችን አስመልክቶ የሰፈነውን የተሳሳተ አተያይ ከማጥራት ባለፈ የሙያ ባለቤት መሆን የክብርና ሞገስ መገለጫ መሆኑን የባለፉት ዓመታት ተሞክሮዎች ያመለክታሉ፡፡ ዜጎች የሙያ ክቡርነትን ተረድተው የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማትን እንዲቀላቀሉ በማነሳሳት በኩልም ይህ ውድድር ትልቅ አስተወፅኦ እንደሚያበረክት የፀና እምነት አለን፡፡

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩትም በሀገራችን የቱሪዝም ዘርፍ ካለው አብርክቶ አንጻር በዘርፉ ብቃት ያለው የሰለጠነ የሰውሃይል ማፍራት ላይ፣ ዘርፉን በጥናትና ምርምር ከማገዝና የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎትን ከመስጠት ባሻገር በየዓመቱ በሚዘጋጁ የቱሪዝም የእንግዳ ተቀባይነት ሳምንት ሰልጣኞች ተሳታፊ የሚሆኑበት ውድድር እየተሰሩ ያሉ ሥራዎችን በዓውደ ርዕይ ማስተዋወቅ፣ የሰልጣኞች የእጅ ሥራ ውጤቶች የሆኑ ምግቦች እና መጠጦች ለውድድር ማቅረብ፣ እንዲሁም የሥራ ዕድል የሚያገኙበትን የሥራና ሠራተኛ መገናኛ መድረኮችን እና ሌሎች ተግባራት የተካተቱበት ነው፡ ፡ ይህ ሁነት ዘንድሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለአራተኛ ጊዜ በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ለ 12ኛ ጊዜ ያከናወነው የክህሎት ሳምንት ውድድር የዚህ ሁነት ማጠቃለያ ድምቀቶች የሆኑ ብቁ ተወዳዳሪዎችን እንድናገኝ እድል የሰጠ ነው፡፡

ውድድሩ በሀገራችን ወጣቶች መካከል ፈጠራን፣ ቴክኒካል ክህሎትን እና የምርምር ልህቀትን የማጎልበት ዓላማ የያዘ ነው፤ ከዚህም ባሻገር በተወዳዳሪዎች መካከል የውድድርና የአሸናፊነት መንፈስ ማዳበሩ፣ በውድድሩ ልቀው የተገኙትን ለሽልማት መብቃት የዚህ ውድድር ስኬት ነው፡፡

ለዚህ ውድድር መሳካት የበኩላችሁን አስተዋጻኦ ያበረከታችሁ እንዲሁም ውድድሩን በስኬት ያጠናቀቃችሁ ሁላችሁንም እንኳን ደስ አላችሁ፡፡ የፈጠራ ሥራዎች የኢትዮጵያን ብሩህ ተስፋና የሚያደርጉ በመሆናቸው ልማትና የፈጠራ ሥራ ለማሳደግ የዘርፉ ተዋናይና የፈጠራ ባለቤቶች በ ትኩረትና በትስስር መስራት ይጠበቅባችኋል፤ መንግስት ለክህሎት ልማት እና የፈጠራ ሥራ የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

አመሰግናለሁ!

ሙፈሪሃት ካሚል

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር



# ክቡር አቶ ጌታቸው ነጋሽ
# የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር መልዕክት

የቱሪዝም ዘርፉ በዓለማችን ከፍተኛ ትኩረት ከተሰጣቸው የልማትና የአገልግሎት መስኮች አንዱ ከመሆኑም ሌላ በየጊዜው ተጨባጭ የሆነ እድገትና ውጤት በማስገንዘብ ላይ የሚገኙ የልማት ዘርፍ ሲሆን ሴክተሩ ለታዳጊም ሆነ ለበለፀጉ አገሮች ሰፊ የስራ እድል በመፍጠር፣ የውጪ ምንዛሪ ገቢን በማሳደግ ዋንኛው የሀብት ምንጭ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል::

በመሆኑም አሁን ባለንበት ዘመን በተጨባጭ ሁኔታ ከማህበራዊ ወደ ኢኮኖሚ ሴክተር በመሸጋገር ላይ ያለ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ ዘርፉ ለሰዎች በርካታ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታዎችን ከማስገኘቱ ባሻገር በሕዝቦች መካከል መልካም ግንኙነትና የባህል ትስስር እንዲኖር ከፍተኛ አበርክቶ አለው::

የሀገራችን የቱሪዝም እና ሆስፒታሊቲ ኢንዱስትሪ፣ ዓለም አቀፍ ደረጃውን ጠብቆ ዘላቂና አስተማማኝ እድገት እንዲኖረው ከማድረግ በዘለለ፣ የሀገራችን መሠረታዊ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮች በዘላቂነት ተቀርፈው፣ የኢትዮጵያ ከዓለም ቀዳሚ የኢኮኖሚ ተርታ ለማሰለፍ ያስችላሉ ተብለው በመንግስት ከተለዩ አምስት ቁልፍ የልማት መስኮች ውስጥ አንዱ የቱሪዝም ዘርፍ እንደሆነ ይታወቃል::

በመሆኑም በመንግስትና በግሉ ዘርፍ እየለሙ ያሉ ተፈጥሯዊ፣ ሰው ሰራሽና ባህላዊ ዘርፈ ብዙ የቱሪስት መዳረሻዎች ማለትም የቱሪዝም ፓርኮች፣ ሪዞርቶች፣ ሆቴሎችና ሬስቶራንቶች በሙያ የሰለጠነ ብቁ የሰው ኃይልና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተደገፈ አሰራር የሚፈልጉ ናቸው::

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ዋንኛው ተልዕኮ በዘርፉ የገበያ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ተግባር ተኮር የክህሎት ስልጠና በመስጠት ሰልጣኞችን ለሀገር ውስጥ እና ለዓለም አቀፍ የሥራ ገበያ ዝግጁ በማድረግ የዜጎች ኑሮና ህይወት እንዲቀየር ብሎም የሆስፒታሊቲ እንዱስትሪው

እንዲዘምን ማድረግ ሲሆን ሌላው ደግሞ ችግር ፈቺ የሆነ የጥናትና ምርምር ማካሄድ እና በዘርፉ ለተሰማሩት ድርጅቶች አስተማማኝና ውጤታማ የሆነ የማማከር አገልግሎት መስጠት ነው፡፡

ኢንስቲትዩቱ ላለፉት ከ50 በላይ ዓመታት በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ በርካታ ሙያተኞችን ሲያፈራ የቆዬ ከመሆኑም ሌላ ለዘርፉ እድገት የራሱን አሻራ ያኖረ ፋና ወጊና የማሰልጠኛ ተቋም ነው፡፡ የማሰልጠኛ ተቋሙ፣ ተጠሪነቱ ለሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሆኖ በአዲስ መልክ ተደራጅቶ ወደ ሥራ እንዲገባ ሲደረግ በመንግስት ከተሰጡት ቁልፍ ተልዕኮዎች ውስጥ አንዱ፣ በሆቴልና ቱሪዝም ሙያዎች መሰልጠን ለሚፈልጉ ዜጎች፣ ጥራትና አግባብነት ያለው የክህሎት ስልጠናን መስጠት የሀገራችን ማዋቅራዊ ችግር የሆነውን የሥራ አጥንት ችግር በዘላቂነት ለመቅረፍ በሚደረገው፣ የራሱን ድርሻ እንዲወጣ እንዲሁም በሀገራችን እያደገ የመጣውን የሆስፒታሊቲ ኢንዱስትሪን በጥናትና ምርምር ደግፎ ለዘርፉ ብቁና ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ሀይል በማቅረብ የኢኮኖሚውን ፍላጎት ማሟላት ነው፡፡

> *... ኢንስቲትዩቱ ላለፉት ከ50 በላይ ዓመታት በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ በርካታ ሙያተኞችን ሲያፈራ የቆዬ ከመሆኑም ሌላ ለዘርፉ እድገት...*

ስለሆነም የማሰልጠኛ ተቋሙ የተጣለበትን ሀገራዊ ኃላፊነት ለመወጣት ከመቼውም ጊዜ በላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ በትብብር መንፈስ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ሆኖም፣ የማሰልጠኛ ተቋሙ የልህቀት ማዕከል ሆኖ የላቀ የክህሎት ስልጠና፣ የላቀ ምርምር እና የላቀ ማማከር አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የሌሎች ባለድርሻ አካላት የላቀ ተሳትፎን ማጎልበት ይጠይቃል፡፡ የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ዘንድሮ 'ብሩህ አዕምሮዎች፣ በክህሎት የበቁ ዜጎች' በሚል መሪ ሀሳብ በአገር አቀፍ ደረጃ ለ4ኛ ጊዜ በተካሄደው የክህሎት ውድድር ላይ በተሳታፊነትና በአስተናጋጅነት የተካፍለን ሲሆን ከፍተኛ ውጤትም አግኝተናል፡፡በተቋም ደረጃ ደግሞ ከሌሎች የዘርፉ ተዋናዮችና ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ለ12ኛ ጊዜ የመሰተንግዶ ሳምንት አክብሯል፡በቱሪዝም ዘርፉ ሙያዊ የክህሎት ውድድር እና የመስተንግዶ ሳምንት በተቋም ደረጃ መካሄድ ከጀመረ እነሆ ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ የክህሎት ውድድሩ ዋና ዓላማ የተወዳዳሪዎቹን በራስ የመተማመን መንፈስ በማጎልበት ፈጠራና ኢኖቬሽንን ለማሳደግ ብሎም ሙያዊ ክህሎት ለማዳበርና የሙያ መሰላልን ለማሻሻል እና በስልጠናና በልምድ የሚገኝ እውቀትና ክህሎት ለማካበት ሲሆን ለሙያው ተገቢውን እውቅናና ማበረታቻ በመስጠት ሙያና ሙያተኛው በማህበረሰቡ ዘንድ እንዲታወቅ ማድረግ ነው፡፡ ከማሰልጠኛ ተቋማት አንጻር ደግሞ በውድድሩ በተገኘው ውጤት የተወዳዳሪዎቹን የአቅም ክፍተት በመለየት የስልጠና ሥርዓትና የስልጠና ጥራቱን ለማሻሻል ዕድል ይሰጣል ተብሎ ስለሚታሰብ በቀጣይ እንደ ሀገር ባህል ሆኖ መቀጠል ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ውድድርና ዝግጅት ተሳታፊ የሆኑ እንዲሁም ላስተባበሩ ሁሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡



## አቶ ገዛኸኝ አባተ
## የሥራ አመራርና አስተዳደር ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር

አቶ ገዛኸኝ አባተ በተቋማዊ ሪፎርምና በክህሎት ውድድሩ ዙሪያ ያስተላለፉት መልዕክት

ሪፎርም የአንድን መስሪያ ቤት አግልግሎት አሰጣጥ ለማዘመን በውስጥም በውጭም ያሉትን ደንበኞች ለማርካት አገልግሎቱ ያለበትን ደረጃ በማጥናት የተሻለ አሰራር፣ አደረጃጀት እና መመሪያዎች በማዘጋጅት ውጤታማ ለውጥ ለማምጣት የሚሰራ ሂደት ነው፡፡
በሀገራችን የሲቭል ሰርቪስ አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል እንደሀገር ሪፎርም ላይ ነን፤ ሪፎርም ላይ ካሉት ሚንስቴር መስሪያ ቤት አንዱ ሥራና ክህሎት በመሆኑ ተቋማችንም እንደተጠሪ ተቋምነቱ ሪፎርም ሥራ ላይ ነው፡፡በተቋማችን የሚሰራው ሪፎርም ምቹ የሥራ ከባቢን መፍጠር ሠራተኛው በተቋሙ ስምንት ሰዓትና ከዛ በላይ ሰዓታት በቢሮ ሲቆዩ ደስተኛ ሆነው እንዲሰሩ ቢሮዎች የማደስ የማስተማሪያ ክፍሎችን፣ ወርክሾፕ፣ የመምህራን ማረፊያ የአመራር እና የአስተዳደር ሰራተኞች ቢሮዎች፣ መጸዳጃ ቤቶች የማደስ እና የመጠገን ሥራ ተሰርቷል።

ሌላው የአሰራር ስርዓትንና መመሪያዎችን በመለየት የዳሰሳ ጥናት በማድረግ በርካታ ሰነዶች እና መመሪያዎች ተሰርተዋል። በቁጥር በአዲስ መልክም የተዘጋጁ መመሪያዎች የተሰሩ ሲሆን አንዳንዶች ላይ ማሻሻያ ተደርጎበታል። አደረጃጀቱም እንደተቋም በቅርብ የተሰራም ቢሆን ተፈትሿል። በመረጃም፣ በሰው ሀብትም መለየት የሚገባው ተለይቶ ከኤጀንሲዎች ጋር በጋራ የሚሰሩ ሥራዎች ተለይተዋል።

ኢንስቲትዩቱ የሚሰጠውን አገልግሎት በመለየት በስልጠና በምርምርና ማማከር፣ ቴክኖሎጂ

ሽግግር እንዲሁም በማህበረሰብ አቀፍ ተቋሙን የሚመስል አደረጃጀትና መዋቅር፤ ሰርቪስ ካታሎግም ተሰርቶ የዝግጅት ምዕራፍ ጨርሰን ወደ ቀጣይ ተሸጋግረናል።

የስልጠና ጥራትን ለማምጣት ከሚያስችሉ ጉዳዮች አንዱ ግብዓት ማሟላት በመሆኑ በመደበኛ በጀት እና በEASTRIP ፕሮጀክት እጅግ በጣም ዘመናዊ የሆኑ በሆቴልና በቱሪዝም ዘርፍ በዓለም ደረጃ አሉ የሚባሉ ዘመናዊ እቃዎችና መጽሐፍት እንዲገቡ ተደርጓል።

ሪፎርሙ ለሰራተኛው ያለው ጠቀሜታ ብዙ ነው፤ ይህም የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚኖረውን ቅሬታ ይፈታል፣ የደንበኛ እርካታን ያመጣል፤ደንበኛ በአገልግሎት አሰጣጣችን ካልረካ አቤቱታውን ተቀብለን ቅሬታውን ፈተን ደስ ብሎት እንዲወጣ እስከ ማድረስ የሚችል አሰራር ፈጥረናል፡፡

ሠራተኛው የተቋሙን ተልዕኮና የተሰጠውን የሥራ ድርሻ በትኩረት ከሰራ በሥራው ስፋት ልክ ጥሩ ተከፋይ እንዲሆንም የሚያስችል ሪፎርም ተሰርቷል፡፡

የሚሰራ ሰው ትክክለኛ ሸልማት ካለው፤ ያጠፋውም በዛው ልክ የሚቀጣ ከሆነ ሰራተኛው ለራሱም በገንዘብም፣ በሞራልም ይረካል፤ ደንበኛውንም ያረካል ማለት ነው።

ህብረተሰቡ የሚያነሳቸውን በአገልግሎት አለመርካት ጥያቄ የሚመለሰው በዚህ ሪፎርም ነው ብለን እናምናለን።

> *... ሠራተኛው የተቋሙን ተልዕኮና የተሰጠውን የሥራ ድርሻ በትኩረት ከሰራ በሥራው ስፋት ልክ ጥሩ ተከፋይ እንዲሆንም የሚያስችል ...*

የዘንድሮውን የክህሎት ውድድርና የእንግዳ ተቀባይነት ሳምንት በተመለከተ ተቋሙ ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚገናኝበት፣ ከኢንዱስትሪው ጋር ሥራንና ሥራፈላጊውን የምናገናኝበት (Jobfair) ዝግጅት፤ ዓመቱን ሁሉ በሁሉም ዘርፎች የተሰሩ ሥራዎች ለዕይታ የሚቀርቡበት እንዲሁም ባለ ድርሻ አካላት የሚሳተፉበት አውደ ርዕይ ይኖራል። ሰልጣኞች ሥራቸውን የሚያሳዩበት ለአጋር አካላት ጋር የተሰሩ ሥራዎች የሚቀርብበበት እና ውይይት የሚካሄድበት ሲምፖዚየም በአጠቃላይ ዓመቱን ሙሉ የተሰሩ ሥራዎቻችን ለዕይታ የቀረቡበት ነው፡፡

በማጠቃለያ ፕሮግራሙ በሀገር አቀፍ ደረጃ በተደረገው ክህሎት ውድድር ተቋማችንን የሚወክሉ ተወዳዳሪዎች ጥሩ ውጤት በማምጣታቸው እየተደሰትን፡፡

ሠራተኞች ሃላፊነታቸውን በመወጣት በዓሉ በደማቅ ሁኔታ እንዲከበር ላበረከቱት አስተዋጽኦ ሁሉንም ከልብ አመሰግናለሁ።



## የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የሥልጠናና ተቋማት አቅም ግንባታ ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር መልዕክት | አቶ ሀብታሙ ክብረት

መስተንግዶ:- የክህሎትና እንግዳ ተቀባይነት ሳምንት ዝግጅት ዓላማን ከሰልጣኞች ተግባር ስልጠና ጋር አያይዘው ቢገልጹልን

አቶ ሀብታሙ:- አንጋፋው ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ረጅም ዓመታት በህብረተሰቡ የሚታወቅ፤ ታላላቅ ባለሙያዎችን ያፈራ ነው:: በመንግስት ለቱሪዝም ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠ ሲሆን ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱም እንደ አዲስ ተልዕኮዎችና ተግባራት ተሰጥቶታል:: በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ የሚያዘጋጀው የቱሪዝምና እንግዳ ተቀባይነት ሳምንት ዋና ዓላማው ለተቋሙ እንደአዲስ የተሰጡትን ተልዕኮዎችና ተግባራትን በማስተዋወቅ የተቋሙን ገጽታ ለመገንባት እና የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ማሳደግ ነው:: ከዚህ በተጨማሪም ሰልጣኞቻችን በተለያዩ ዘርፎች የክህሎት ውድድር በማድረግ በመካከላቸው የፉክክር መንፈስ እንዶኖር በማድረግ ጥራት ያለው ሰልጣኝ ለማውጣት የሚጠቅም ሲሆን አሰሪና ሰራተኞች የሚገናኙበት መድረክም ሆኖ አገልግሏል:: ተቋሙ ውስጥ በነበረው ውድድር አሸናፊ የሆኑ ሰልጣኞች በሀገር አቀፉ የክህሎት ውድድር ላይ በመሳተፍ ጠንካራ ተወዳዳሪ ለማውጣት ዕድል ፈጥሯል::

መስተንግዶ:- የክህሎትና እንግዳ ተቀባይነት ሳምንት ዝግጅት ባለፉት ጊዜያት ከተከበረበት አንጻር ዘንድሮ ምን የተለየ ፕሮግራም አለ?

አቶ ሀብታሙ:- በየሁለት ዓመቱ ሀገር አቀፍ የክህሎት ውድድር ይዘጋጃል፣ በተቋማችን ደረጃ በየዓመቱ እናዘጋጃለን፣ አስተሳሰቦች እያደጉ ፣ ነባራዊ ሁኔታዎች እየተቀየሩ ይሄዳሉ:: ስለዚህ ከወቅቱ ጋር የሚስማማ ፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እና ከህረተሰቡ እንዲሁም ሰልጣኞቻችን እድገት ደረጃን የሚመጥን የቱሪዝምና እንግዳ ተቀባይነት ሳምንት ነው::

**መስተንግዶ:-** ከተግባር ስልጠና አንጻር በስልጠናና አቅም ግንባታ ዘርፍ ከባለፉት ጊዜያት የተሻለ ምን እየተሰራ ነው?

**አቶ ሀብታሙ:-** የዘንድሮው የቱሪዝምና እንግዳ ተቀባይነት ዝግጅትን ከሌላ ጊዜ የሚለየው ዘንድሮ እንደተቋም የISO 21001/18 ዓለም አቀፍ የትምህርት ጥራት ትግበራ መጀመራችን እና የሲቪል ሰርቪሰስ ሪፎርም እየሰራን መሆናችን ብቃት ያለው የሰው ሀይልን ለማፍራት፣ ጥራት ያለው የኢንዱስትሪውን ፍላጎት የሚያሟላ ስልጠና እየሰጠን ነው፡፡ ያሉን የስልጠና መርሐ ግብሮች ጥናትን መሰረት በማድረግ የኢንዱስትሪውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ስልጠና እየሰጠን እንገኛለን፡፡ ስለዚህም ሰልጣኞችን ስንቀበል በፍላጎትና በዝንባሌያቸው እንዲሆን የሳይኮሜትሪክ ቴስት በመውሰድ አብላጫ ውጤት ባመጡበት ዘርፍ እንዲማሩ በአቻ ግፊትም ትህርት መስካቸውን አንዳይቀይሩ በፍጹም ፍላጎት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ነው የተደረገው፡ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ በሆስፒታሊቲ ኢንዱስትሪው ውስጥ በቋንቋ ብቁ የሆኑ ሰልጣኞችን ለማውጣት አዲስ ሰልጣኞችን ሲቀበል የቃልና ጽሁፍ ፈተና በመስጠት እና እንግሊዘኛ ቋንቋ አራት ወሰነ ትምህርት እንዲማሩ ተደርጓል፤ ከዚህ በተጨማሪም አረብኛ፣ ፈረንሳይኛና ጀርመንኛ በተለመደው አኳኋን ስልጠና እየተሰጠ ይገኛል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የኢንተርሪነርሺፕ ስልጠና እንዲወስዱ ማድረግ ሰልጠኞች ስራ ፈጣሪ እንዲሆኑ የሚረዳቸው ሲሆን መልካም ስነምግባርም እንዲኖራቸው የሙያዊ ሥነ ምግባር እየተሰጠ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ ሰልጣኞች የሃርድ ስኪል ብቻ ሳይሆን የልል ችሎታቸው(ሶፍት ስኪል) ብቁ እንዲሆኑ እየተሰራ ነው፡፡

> *... በአጠቃላይ ሰልጣኞች የሃርድ ስኪል ብቻ ሳይሆን የልል ችሎታቸው(ሶፍት ስኪል) ብቁ...*

ሌላው ከባለፉት ጊዜያት በጣም የሚለይ ተግባር የተግባር ስልጠና በኢንዱስትሪ ውስጥ የሥራና ክህሎትሚኒስቴርባወጣውመመሪያ መሰረት 70% በአግባቡ እያሰለጠንን እንገኛለን፡፡ ሰልጣኞች በሆቴልና ቱሪዝም ድርጅቶች ውስጥ የተግባር ስልጠናቸውን ሲከታተሉ 30% ውጤት በኢንዱስትሪ አሰሪዎች ይሞላል፡፡ በኢንዱስትሪው ውጤት መሞላቱ ሰልጣኞች ያለአግባብ ጊዜያቸውን እንዳያባክኑ የሚያግዝና ኢንዱስትሪውም ስልጠና ላይ እንዲሳተፍ እያደረገ ይገኛል ማለት ነው፡፡

**መስተንግዶ:-** በመጨረሻ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

**አቶ ሀብታሙ:-** ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ታላላቅ ባለሙያዎችን ያፈራ በመሆኑ በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ብንሄድ ሰልጣኞቻችንን እናገኛለን፡፡ ስለሆነም እንኳን ለ12ኛው የክህሎት ውድድርና እንግዳ ተቀባይነት ሳምንት አደረሳችሁ እያልኩ ይህ ዝግጅት በጥሩ ውጤት እንዲጠናቀቅ በዚህ ውድድርና ዝግጅት ተሳታፊ የሆኑ እንዲሁም ላስተባበርሩ አካላት ምስጋና ማቅረብ እፈልጋለሁ፡፡



አቶ ይታሰብ ሥዩም የኢንስቲትዩቱ የጥናት ምርምርና ማማከር ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር መልዕክት

መስተንግዶ፡- የክህሎትና እንግዳ ተቀባይነት ሳምንት ዝግጅት ዓላማን ከጥናትና ምርምር ጋር አያይዘው ቢገልጹልን

አቶ ይታሰብ፡- ተቋማችን ላለፉት ከአስር ዓመታት በላይ ሲከናወን የቆየው የመስተንዶ ሳምንት በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ከክህሎት ውድድር ጋር ነው እያከበርን ያለው፡፡ ይህ የክህሎት ውድድር በሀገር አቀፍ ደረጃ በየሁለት ዓመቱ የሚካሄድ ነገር ግን በኛ ተቋም ውስጥ የመስተንግዶ ሳምንቱን በየዓመቱ ከክህሎት ወድድር ጋር ደግሞ በየሁለት ዓመቱ በማቀናጀት እያዘጋጀን ነው፡፡ በዚህ ሁነት ውስጥ በርካታ መርሐ ግብሮች አሉ፣ ለሶስት ቀን የሚዘጋጅ ቢሆንም እንኳን የቱሪዝምና መስተንግዶ ዘርፉን ባለድርሻ አካላት ለማሰባሰብ ትልቅ እድል ይሰጠናል፣ በዚህም ባለድርሻ አካላት በአንድ ቦታ ሲሰባሰቡ ልምዱን እውቀቱን እንዲሁም በአጠቃላይ በዘርፉ ያለውን አጀንዳዎች ዙሪያ ውይይት ለማድረግ እድል የሚፈጥር ነው፡፡ እንደ ጥናትና ምርምር ዘርፍ ሁልጊዜ እንደሚታወቀው በተመረጡ መረቃሎች ላይ የተመሰረተ የፓናል ውይይት ይደረጋል፡፡ በየዓመቱ የምናዘጋጀው በርካታ ፓናል ውይይቶች ቢኖሩም ይህን የመስተንግዶ ሳምንት ምክኒያት በማድረግ አንድ ፓናል ውይይት ይዘጋጃል፡፡ ይህ መድረክ የዘርፉ ምሁራን፣ ሰልጣኞች፣ ባለድርሻ አካላት፣ ባለሀብቶች የሚሳተፉበት ነው፡፡ ከፍተኛ የሆነ የእውቀት ሽግግር የሚደረግበት ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ሃሳቦች የሚነሱበት መድረክ ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ከክልሎች ጋር በመተባበር የምናጠናቸው የባህል ምግቦች ከሌሎች ባለድርሻ ጋር በመነጋገር የባህል ምግብ ፌስትቫል የሚዘጋጅበት ነው፡፡ ይህ በሁሉም ክልሎች ላይ የምናደርገው የባህል ምግብ ጥናት ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ነው፡፡ እዚሁ አዲስ አበባ ይህ ሲዘጋጅ የሚፈልጉ ሆቴሎች ግብዓቶቹ እዚሁ መገኘት እንደሚችል በመረዳት ወደ ሜኑ እንዲቀይሩ ይረዳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሰነድ ብቻ ከመስጠት ምግቡን አቀራረቡን እዚሁ አይቶ መነሳሳትን ይፈጥርላቸዋል፡

ሶስተኛው በሀገር አቀፉ የክህሎት ውድድር ላይ በተግባራዊ ምርምር እና በቴክኖሎጂ ሰልጣኞችና አሰልጣኞች ተሳተፉበት የቴክኖሎጂ ውድድር ተደርጓል፡፡ የቴክኖሎጂ ውድድር ከኮምፒተር ጋር የተያያዙ ሲሆን የህብረተሰቡን ችግር የሚፈቱ ምርምሮችም ተመርጠው በሀገር አቀፉ ውድድርና እውቅና የተሰጠበት ነው፡፡ ተግባራዊ ምርምር ተቋማዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መምህራን ፣ሰልጣኞች ተመራማሪዎች ችግር ፈቺ የሆኑ ምርምሮችን ያደረጉበት ሁለቱም አዲስ ዘንድሮ የተጀመሩ ናቸው፡፡

ሌላው የበጎ አድራጎት ስራ ሲሆን ከሌላ ጊዜ የሚለይበት በመቄዶንያ ድጋፍ በማድረግ ሀብት የተሰበሰበበት እንዲሁም የስራ ቅጥር አውደርዕይ በማካሄድ ተመራቂ ሰልጣኞቻችን ከቀጣሪ ድርጅቶች ተገናኝቶበታል:: የዘንድሮው የክህሎት ውድድርና እንግዳ ተቀባይነት ሳምንት በጥናት፣ በምርምር፣ በማማከር እና በማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት የተሰሩ ስራዎችን የታዩበት ነው:: ይህ ሌሎች ጋር ለመቀራረብ ትልቅ እድል የፈጠረ መድረክ እንደሆነ እናምናለን::

መስተንግዶ:- የክህሎትና እንግዳ ተቀባይነት ሳምንት ዝግጅት በጥናትና ምርምር ዘርፍ ምን የተለየ ያደርገዋል?

አቶ ይታሰብ:- ለየት የሚያደርገው ከዚህ በፊት ያልነበረ በቴክኖሎጂና ተግባራዊ ምርምር ውድድር መጀመራችን ልዩ ያደርገዋል:: ሁለተኛ የባህል ምግብ ፌስትቫል ከተባባሪ አካላት ጋር ለማክበር ዕቅድ አለን:: ሶስተኛ የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎቶችን አዳዲስ ነገሮችን ጨምረንበታል::

መስተንግዶ:- በማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ እየተሰሩ ያሉ ጥናቶችን ወደ ተግባር ከማስገባት እና በሌሎች አካላት ያልታዩ ጥናቶችን ከመስራት አንጻር ከባለፉት ጊዜያት የተሻለ ምን እየተሰራ ነው?

አቶ ይታሰብ:- ከዓመት ዓመት መሻሻሎች አሉ:: ከበርካታ ባለድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ እየተፈራረምን ነው:የጋራና በቅንጅት የሚሰሩ ጥናትና ምርምር ስራዎች ትላልቅ ችግሮችን ሊፈቱ የሚችሉ ስራዎችን እየሰራን ለህብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ሊያስገኙ የሚያስችሉ ስራዎች እየተሰሩ ነው::
ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተፈራረምናቸው የጋራ መግባቢያዎችም ይህኑ ለመተግበተር የሚያስችሉ ሲሆን ተቋሙ እየሰራ የሚገኙ ጥናቶች መፍትሔ አመላካች እንዲሆኑ ነው ጥረት እየተደረገ የሚገኘው:: በቅርብ ጊዜ ከተሰሩ ምርምሮች መካከል ፖሊሲ ሊወጣባቸው የሚችሉ ጥናቶችን በማቅረብ በከፍተኛ ሁኔታ የታየ ጥናት አለ:: (በዘርፉ ያለው የሰው ሀይል ጥናት) በዚህ ጥናት መሰረት 48% ብቻ በሆቴልና ቱሪዝም ሙያዎች ሰልጣኞች ዘርፉ ላይ እየሰራ ይገኛል:: በዚህ መሰረት በልምድ የተገኘን እውቀት ብቃት ማረጋገጫ የመስጠት ሥራዎች ለመተግበር ከዘርፉ ባለድርሻ መ/ቤቶችና ማህበራት ጋር ውይይት እየተደረገ ነው:: ስለዚህ የጥናቱ ውጤት ወደ ተግባር እየተቀየረ ይገኛል::

መስተንግዶ:- ተቋሙ በሚያዘጋጃቸው የጥናትና ምርምር ውጤቶች ላይ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ምን ይመስላል?

አቶ ይታሰብ:- የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ ነው የመጣው:: ዘርፉ ከግል እስከ መንግስት ተቋማት ድረስ በርካታ ባለድርሻ አካላት ያለው ነው:: ቱሪዝም ሚኒስቴር ፣ ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ የሚኒስቴሩ ተጠሪ ተቋማት፣ የግል ዘርፉ ሆቴሎች ፣ የአስጎብኝ ድርጅቶች ፣ ማህበራት፣ የምርምር ተቋማት፣ የክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች እና ማህበረሰቡም ጭምር ባለድርሻ ናቸው:: ባለድርሻ የሚያስፈልገው ውጤታማ ለመሆን ነው:: በተለይ የዘርፉን ተቋማት የማማከር አገልግሎት ስንሰጥ የኢንዱስትሪ ባለሙያዎች ተሳትፎ ነበር:: ይህ በባለሙያዎቹ መካከል የልምድ ልውውጥን የሚያስገኝ ለማህበረሰቡም ትክክለኛ አገልግሎት ለመስጠት ያስቻለን ትልቅ ተሞክሮ ያገኘንበት ነው::

መስተንግዶ:- በመጨረሻ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

አቶ ይታሰብ:- የቱሪዝምና እንግዳ ተቀባይነት ሳምንት የማሰልጠኛ ኢንስቲትዩታችን መለያ ነው:: ይህን በየዓመቱ የተለያዩ ሁነቶችን በማካተት ከፍ እያለ የመጣ ሁነት ነው:: ስለዚህ ዘንድሮ በተካሄደው ዝግጅት ላይ የተቋማችን ማህበረሰብ፣አሰልጣኞች፣ ሰልጣኞችና ባለድርሻ አካላት ሁሉ ላደረጉት የነቃ ተሳትፎ ምስጋና ማቅረብ እወዳለሁ::



# “ከልጅነት እስከ እውቀት በመምህርነት”

## ቆይታ ከመምህርት አንለይ ሙሉጌታ ጋር

መስተንግዶ:- በቅድሚያ ለቃለመጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑ ከልብ እናመሰግናለን!

ወ/ሮ አንለይ :- እኔም ለዚህ ቃለመጠይቅ ስለጋበዛችሁኝ አመሠግናለሁ!

መስተንግዶ:- ስለአስተዳደግዎ፣ ስለትምህርትና ሁኔታ እና ስለ ቤተሰብዎ ሁኔታ ይግለጹልኝ?

ወ/ሮ አንለይ :- አባቴ አስተማሪ እናቴ ደግሞ የቤት እመቤት ናት እኔ ለቤቱ የመጀመሪያ ልጅ ስሆን ብቸኛ ሴት ልጅም ነኝ ከታናናሽ ወንድሞቼ እኩል በነፃነት አድጌያለሁ::

ወላጆቼ በተለይ አባቴ ደፋርና በራስ መተማመን እንዲኖረኝ፣ ሰውን እንዳከብር እንጂ እንዳልፈራ አርገው ነው ያሳደጉኝ። በትምህርት አቀባበሌ ፈጣንና ጎበዝ ከሚባሉት የምመደብ ስሆን ከዲፕሎማ እስከ ሁለተና ዲግሪ ደርሻለሁ::

በዚሁ ኢንስቲትዩት በነበረኝ ቆይታም በትምህርት በጣም ስለማምን Hotel Management Degree በከፍተኛ ማዕረግ ተመርቄአለሁ። ሁለት ሴት ልጆች አሉኝ እነሱም በትምህርታቸው ጥሩ ውጤት አምጥተው የዩንቨርሲቲ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ::

መስተንግዶ:- እርስዎ መምህርነትን እንዴት ይገልጹታል?

ወ/ሮ አንለይ :- አባቴ መምህር መምህር ነው:: በዚያን ወቅት ደግሞ መምህርነት ትልቅ ክብር አለው። የመምህር ልጅ መሆኑ በራሱ በጣም የሚያኮራ ነበር። ይህ በመሆኑ ከልጅነቴ ጀምሮ መምህር መሆን ምኞቴ ነበር ለዚህም ነው ለረዥም ጊዜ በማስተማር ላይ የቆየሁት።

12ኛ ክፍል እንደጨረስኩ ምደባም የደረሰኝ ዓለማያ እርሻ ኮሌጅ STTP/Science Teachers Training Program / በኬሚስትሪ መምህርነት ነው የተመረቅሁት።

አሁንም መምህርነት የሚሰጠው ክብር እንደበፊቱም ባይሆን ከነችግሩ ሙያው የምወደው ነፃነት ያለው ሥራ ነው ::

የትም ቦታ ያስተማርኳቸውን በተለያየ የሙያ መስክ ተሰማርተው ሳይ ደስታና ኩራት ይሰማኛል። መምህርነት የተከበረ ሙያ ሲሆን ትውልድን የሚቀርፅና የአንድ ሀገር እድገት የሚያመጡ ባለሙያዎችን የሚያፈራ ነው። Really I Love it.

መስተንግዶ:- ሴት ነዎት ልጆችዎም ሴቶች ናቸው ማህበረሰቡ ደግሞ ስለሴቶች ያለው አመለካከት አለ እርስዎ ይህን ቻሌንጅ እንዴት አለፉት ለልጆችዎስ እንዴት እንዲሆኑ ነው የሚመክሯቸው?

ወ/ሮ አንለይ :- በእርግጥ በተለይ በፊት

ማህበረሰቡ ለሴት ልጅ ያለው አመለካከት የተዛባ ነበር። አሁን የተሻለ ቢሆንም ችግሩ ሙሉ በሙሉ ተቀርፏል ማለት ግን አይቻልም። እኔ ይህ አመለካከት ሰብሬ መውጣት የቻልኩት ሥራ በመሥራት በሁሉም ነገር ላይ እኩል በመሳተፍ ፣በመወያየት ሀሳቤን በግልፅ በማጋራት እና ባለመፍራት የተወጣሁት ይመስለኛል። ልጆችንም ሳሳድግ ደፋር ሰነ ስርዓት ያላቸው እና በራስ መተማመን እንዲኖራቸው እያደረኩ ነው፡፡ በትምህርታቸው ፣ ባላቸው ተሳትፎ ሁሉ ጎበዝ እንዲሆኑ፤ ሰውን ማክበር እንጅ መፍራት እንደሌለባቸው እመክራቸዋለሁ። እግዚአብሔር ይመስገን ይህም የተሳካልኝ ይመስለኛል።

መስተንግዶ:- ሴቶች ምን እንዲሆኑ ይመክራሉ?

ወ/ሮ አንለይ :- እኔ ሴቶች ጠንካራ ፣ ደፋር፣ ስነ_ ስርዓት ያላቸው እንዲሁም በራስ መተማመን ያላቸው እንዲሆኑ እመክራለሁ። በዞውን ጊዜ ለቅሶ የሴቶች የስሜት መግለጫ ተደርጎ ነው የሚሳለው፤ ሴቶች ስሜታቸውን በውይይት እንጅ በለቅሶ እንዳይገልፁ አደራ እላለሁ።

መስተንግዶ:- በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስትቲዩት የነበረዎት ቆይታ ምን ይመስላል?

ወ/ሮ አንለይ :- በተቋሙ የነበረኝ ቆይታ በጣም ጥሩ አሰደሳችና ብዙ ሥራ የሰራሁበት ነው። ኢንስቲትዩቱ ውስጥ ባለኝ የሥራ ቆይታ አብዛኛውን የሀገሬን ክፍል የማየት እድል አግኝቻለሁ፡፡ በቆይታዬ በሃላፊነት አገልግያለሁ፣ በተመደብኩባቸው የኮሚቴ ሥራዎች ውስጥም በትብብር በርካታ ሥራዎችን መሥራት ችያለሁ፣ ልምዴን አካፍያለሁ ISO ላይም ያለኝ አበርክቶ በጣም ጥሩ ነው ኢንስቲትዩቱ የ ISO በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እንዲያገኝ ምኞቴ ነው።

መስተንግዶ:- ተቋሙ አሁናዊ ሁኔታ እና ቀድሞ ከነበረው ተሞክሮ ስልጠና አሰጣጡንም ያውቁታል ምን ቢሻሻል፣ ቢቀጥል፣ ጭራሽም ባይኖር የሚሉት ነገር ካለ ቢገልጹልን ?

ወ/ሮ አንለይ :- በተቋሙ በእርግጥ ብዙ ሥራ ይሰራል፤ ግን መረጃ አያያዝ ላይ ችግር አለ። ይህንን አሁን ISO ተግባራዊ እየተደረገ ስለሆነ የነበሩት ችግሮች ይቀረፋሉ ብዬ አምናለሁ። ወደፊት በተሻለ ሁኔታ የቱሪዝም ዘርፉን የሚደግፍ ይሆናል ብዬ አስባለሁ። የሥልጠና ሂደቱ ትንሽ ቁጥጥር ተደርጎ ሠልጣኞቻችንን በአግባቡ አሰልጥነን ተወዳዳሪ ማድረግ ይጠበቅብናል።

መስተንግዶ:- መምህርነት ትውልድን መቅረጽ፣ መገንባት ነው በዚህ የረጅም ዘመን አገልግሎት ገጠመኝ አይጠፋምና ቢያካፍሉን ?

ወ/ሮ አንለይ :- ብዙ ይኖራሉ የማልረሳው ገና ሥራ እንደጀመርኩ አንድ ተማሪ አባቴ ሞተብኝ ብሎ አስፈቀደኝ እኔም አዝኜ አይዞህ እግዚአብሔር ያፅናህ ብዬ ፈቀድኩለት። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ይኼው ተማሪ አባቴ ሞተብኝ ፈቃድ ስጭኝ ብሎ ሲጠይቀኝ ትኩር ብዬ አየሁትና ምነው አንተ ከዚህ በፊት አባቴ ሞተብኝ ብለህ አስፈቅደህ አልነበር እንዴ ስለው በማወቄ ደንግጦ ውይ ሚስ አረስቼ ነው ከዚህ በፊት አስፈቅጀበታለሁ እንዴ? ብሎ እኔኑ የጠየቀኝን ተማሪ አልረሳውም።

መስተንግዶ:- ለኢንስቲትዩቱ ምን ይመኛሉ ?

ወ/ሮ አንለይ :- ኢንስቲትዩቱ ያስቀመጠውን ራዕይ ተሳክቶለት ማየት እመኛለሁ።

መስተንግዶ:- ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ ?

ወ/ሮ አንለይ :- አሠልጣኞች ሠልጣኞቻቸው ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ መትጋት አለበቸው፡ ፡ ሠልጣኞቻችንም ጊዜያቸውን በአግባቡ በመጠቀም የተቋሙን ስርዓት ጠብቀው ሠልጥነው ተፎካካሪ ባለሙያዎች እንዲሆኑ፤ ከሁሉም በላይ የተቋሙ አመራር የሥልጠናው ጥራት እንዲጠበቅ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል እንዲያደርግ መለክቴን አስተላልፋለሁ፡፡

መስተንግዶ:- ለሰጡን ጊዜ እናመሰግናለን !!

ወ/ሮ አንለይ :- እናንተንም ይህን ዕድል ስለሰጣችሁኝ አብዝቼ አመሰግናለሁ!!

# እንግዳ



ወ/ሮ ሳምራዊት ሞገስ ይባላሉ፡፡ሀገራችንን በቱሪዝም ዘርፍ ከሚያስተዋውቁ ድርጅቶች የአንጋፋው ትራቭል ኢትዮጵያ መስራችና ባለቤት ናቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በኢንስቲትዩቱ የአማካሪ ቦርድ አባል ሆነው በማገልገል ላይ የገኛሉ ከወ/ሮ ሳምራዊት ጋር ስለ ህይዎተ ተሞክሯቸው ስለ ቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ አሁን ያለበትን እና የወደፊት ምን መምሰል አለበት በሚሉ ሃሳቦች ዙሪያ ቆይታ አድርገናል መልካም ንባብ፡፡

መስተንግዶ፡- በቅድሚያ ስለሰጡን ጊዜ ከልብ እያመሰገንን ራስዎን ያስተዋውቁን

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ትምህርቴን እንደጨረስኩ በብሔራዊ አስጎብኝ ድርጅት የመጀመሪያ ሥራዬን ጀመርኩ፡፡ ያጠናሁት ጋዜጠኝነት ነው፣ ብሔራዊ አስጎብኚ ድርጅት ደግሞ የቱሪዝም ልምድ እንዲኖረኝ አድርጓል፡ ለእኔ እንደ ትልቅ የቱሪዝም ማሰልጠኛ ተቋም ነው የማየው፡፡

ምክኒያቱም በጊዜው በነበሩ መልካም አለቆች ስለቱሪዝም ብዙ እውቀት ያገኘሁበት ስለሆነ፡፡ ብሔራዊ አስጎብኝ ድርጅት በወቅቱ እስከ 1991 ድረስ ብቸኛ አስጎብኝ ድርጅት ነበር፣ ልክ የቅልቅል ኢኮኖሚ ሲፈቀድ በ1993 ከብሔራዊ አስጎብኚ ድርጅት በመልቀቅ በ1994 ከባለቤቴ ጋር ሆነን ትራቭል ኢትዮጵያ ድርጅት መሰረትን፡

> መልከ ብዙ ፤መስህበ ብዙ ኢትዮጵያን በሚገባ አላስተዋወቅናትም፡፡
>
> ወ/ሮ ሳምራዊት ሞገስ

፡ ሰላሳ ዓመት የሞላው ድርጅት ነው ትራቭል ኢትዮጵያ፡፡

መስተንግዶ፡- የቱሪዝም ኢንደስትሪን እንዴት ይገልጹታል?

ወ/ሮ ሳምራዊት፡- የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ከማንኛውም ሴክተር በጣም ፈጣን፣ ገቢ የሚያስገኝ፣ በጣም ብዙ የሥራ እድል መፍጠር የሚችል፣የሃገርን ገጽታ ለመገንባትና ኢኮኖሚ ለማሳደግ የሚያስችል ዘርፍ ነው፡፡ ቱሪዝም ለአንድ ሀገር ምን ማለት እንደ ሆነ ይታወቃል፤ ቱሪዝም ስንል እንደ አስጎብኝ ያለውን ሁኔታ ስናይ ቀደም ሲል በዓለም ላይ በ2019 ኮቪድ ምክኒያት ወደኋላ የቀረባቸውን የቱሪዝም ስራ የዓለም ሀገራት በከፍተኛ ሁኔታ እያስፋፉ ያለበት ሁኔታ ይገኛል፡፡ እንደ ሀገራችን ደግሞ ከኮቪድ በኋላም ቢሆን ያለው የሃገራችን የሰላም ጉዳይ ቱሪስቶችን ደፍረን ኑ የማንልበት፣ ወደኋላ የቀረንበት ነው፡፡

መስተንግዶ፡- የ(EASTRIP)ሃገራችን የቱሪዝም ዘርፍ ለመደገፍ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ምን ማቀድና መሥራት አለብን ብለው ያምናሉ?

ወ/ሮ ሳምራዊት፡- እንደ ሀገር አንዳንድ ጊዜ እርዳታዎች ይመጣሉ፣ ይህን እርዳታ ከንግግር ባለፈ መሬት ወርዶ ወደ ተግባር ልንቀይራቸው የሚገቡ ነገሮች ናቸው፡፡ እንደ EASTRIP ቴክኒካል አማካሪ ኮሚቴ በጽሁፍም ሆነ በንግግር የምንለዋወጣቸው ሀሳቦች አሉ፣ ይህን ለማሳካት የተግባር ሰዎች መሆን አለብን፡እንደ ሀገር ምንድነው የጎደለን? የሚለውን በጋራ እንድናይ ያደረገን ነገር አለ፣ ለዘርፉ ማበርከት የምንችለው፣ የጸጥታ ችግር አለ ተብሎ እጃችንን አጣጥፈን የምንቀመጥበት ጊዜ አይደለም፡፡ ስለዚህ ሁሉም የቤት ስራውን የሚሰራበት ሁኔታ ሊኖር ይገባል፡፡

መስተንግዶ፡- እርስዎ በቱሪዝም ዘርፍ ካሎዎት የሙያ ልምድ አንጻር በአማካሪ ቦርዱ ውስጥ ምን እያገዙ ነው?

ወ/ሮ ሳምራዊት፡- የአማካሪ ቦርዱ አባል ነኝ፡፡ በአባልነት ባለኝ የሙያ ዘርፍ ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩትን ሊያሳድጉ የሚችሉ ሃሳቦች ላይ ከቡድኑ አባላት ጋር ጥልቀት ያለውን ውይይት በማድረግ በጽሁፍ እያቀረብን እንገኛለን፡፡ ተነጋግረን መሻሻል ያለባቸው፣ መጠናከር አለባቸው ብለን ያቀረብናቸው ሃሳቦች ተስፋ አለን፣ ነገሮች ወደ ተግባር ይቀየራሉ፡፡
ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ይህን ሁሉ ዓመት ሲያሰለጥን አሉ የምንላቸው ጉድለቶች እና ጠንካራ ጎኖች አሉ፣ ብቃት ያለው ባለሙያ ማፍራት ላይ አጥብቀን እንድንሰራ እንመክራለን፡



**መስተንግዶ:-** ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ብቁ ባለሙያዎችን አሰልጥኖ ከማውጣት ጋር በተያያዘ አሁንና ወደፊት ምን ቢሰራ ለትውለዱ የተሻለ ነው ብለው ያምናሉ?

**ወ/ሮ ሳምራዊት:-** በመጀመሪያ ደረጃ በየትኛውም የትምህርት ተቋም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ እውቀት ያላቸው፣ ተማሪዎችን ሊለውጡ የሚችሉ አስተማሪዎች መኖር በጣም መሰረታዊ ነው:: ስለዚህ ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ያሉት አሰልጣኞች ምን ያህል ብቁ ናቸው፣ በእውቀትና ክህሎት፣ በማስተማር ስነ ዘዴ ያላቸውን ብቃት እየገመገመ መሄድ አለበት:: ተቋሙ ከዚህ በፊት በጣም ጠንካራ መምህራን የነበሩበት ነው::

አሁንም ተቋሙ እራሱን እያሳደገና እያበቃ መሄድ፣ የሚያፈራቸው ሰልጣኞች የዳበረ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ያላቸው እንዳሉ ሁሉ ጉድለት የሚታይባቸውንም የተለያዩ የስልጠና መርሐ ግብሮችን በማዘጋጀት ብቁ እንዲሆኑ መስራት ይጠበቅበታል:: በሌላም በኩል በቋንቋ፣ በአመራር ክህሎት፣ ራስን መግለጽ እና ሌሎችም የአጫጭር ጊዜ ስልጠና ከሚሰጡ ድርጅቶች ጋር አብሮ ቢሰራ ጥሩ ነው::

> ... የመጀመሪያው አጠቃላይ ለአካባቢው ማህበረሰብ ፕሮጀክቶቹ ይዘውት የመጡትን ቱርፋት ግንዛቤ እንዲፈጥሩ ማድረግ...

**መስተንግዶ:-** እርስዎ በቱሪዝም ዘርፍ አሁን ያለውን ሀገራዊና ዓለማቀፋዊ ገጽታ እንዴት ያዩታል?

**ወ/ሮ ሳምራዊት:-** የኢትዮጵያ ቱሪዝም አድጓል ማለት አልችልም:: አንዱ የእድገት ምልክት መሰረተ ልማት ነው:: መሰረተ ልማት የቱሪስት ፍሰትን ይጨምራል:: ሀገራችን ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ጋር ስናነጻጽራት የመስህብ ደሃ አይደለችም፣ መልከ ብዙ፣መስህበ ብዙ ናት:: እኛ ይህን ሁሉ መስህብ ይዘን ዓመቱን ሙሉ ማስጎብኘት ሲገባን ይህ እየሆነ አይደለም :: ሀገራችን ላይ የተፈጠሩ የእርስበዕርስ ጦርነትና ከዚያ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች በዘርፉ የሚደረገውን ኢንቨስትመንት እንዲቀንስ አድርጓል:: ለተከሰቱ ችግሮች እውቅናም አልተሰጠም፣ የተደረገ ድጋፍም የለም:: መንግስት በዘርፉ የሚሰማሩትን መደገፍና ኃላፊነት መውሰድ አለበት:: ሌላው በዘርፉ ያሉትን ችግሮች በየጊዜው ተለይቶ የሚቀርብ ቢሆንም በተለይ በሚኒስትር ደረጃ ያሉ ኃላፊዎች መለዋወጥ እና ሁሉን ነገር እንደ አዲስ መጀመር የተለዩ ተግዳሮቶች ወደ ተግባር እንዳይቀየሩ አድርጓል የሚል እምነት አለኝ:: የሀገራችንን ቱሪዝም ከሚያስተዋውቁት መካከል አንዱና ዋናው አየር መንገዳችን ነው::

በተለይ በኮቪድ ወቅት ዓለም ላይ ተደራሽ የነበረው አየር መንገዳችን ብቻ ነበር:: እኔ ሁሌ የሚገርመኝ የኢትዮጵያ አየር መንገድ እንዲህ ማደግ ከቻለ የኛ የቱሪዝም ዘርፍ ለምን አላደገም? አብዛኛው ትራንዚት አድርጎ ወደ ሌላ ሀገር እያለፉ ነው፣ አዲስ አበባ ውስጥ የሚቀር ቱሪስት የለም:: ግንዛቤ ስላልፈጠርን ነው? በቂ ማስታወቂያ ስላልሰራን ነው? ኢምባሲዎቻችን ኢትዮጵያን ለማስተዋወቅ ምን ያህል እየሰሩ ነው? የአፍሪካ ሀገሮች ስንሄድ ለምሳሌ ኬንያ በዓለም ላይ ሀገራቸውን የሚያስተዋውቁበት ብዙ ቢሮዎች አሏት::

እስካሁን ድረስ ለቱሪዝም ተብሎ የተከፈተ ቢሮ የለንም፤ በኢምባሲዎቻችን ያን ያህል ትውውቅ አለ ብዬ አልገምትም:: ጥሩ ሥራ ማስታወቂያ አያስፈልገውም የሚባለው ነገር ድሮ ቀረ አሁን በጣም ማስተዋወቅ አለብን::

በማህበራዊ ሚዲያው የሚሰራጩ እንደ ሀገር አሉታዊ ነገሮችን በአግባቡ እንኳን መልስ አይሰጥባቸውም:: ይህን ሥራ መንግስት ሥራዬ ብሎ ፕሮግራም አድርጎ ሊሰራበት ይገባል::

በነገራችንላይይህበግሉዘርፍየሚሰራአይደለም:: ከሌሎች ብዙ ልንማር ይገባል፤ ሁልጊዜ ይጽፋሉ፣ ራሳቸውን ያስተዋውቃሉ:: እኛ ደግሞ ማስተዋወቅ ላይ ድክመት አለብን፣ በዚህ ላይ ደግሞ የጎብኚዎች ቁጥር እንኳን በትክክለኛና ታማኝነት ባለው መልኩ የሚታወቅበት ጊዜ የለም:: እንዴት ነው ዘመናዊ አድርገን መስራት የምንችለው? ይህችን ውብ ሀገር ብዙ ሀብት ይዘን ቱሪዝሙን አለማዘመን አሳዛኝ ነው ለምሳሌ ኮንፍረንሶች አዲስ አበባ ቢደረጉ ይቻላል፤ ግን በግፊት(lobby)ወደ ሌላ ሀገር እየሄደ ይገኛል ይሄንን እንዴት ነው የምናስቆመው? አዲስ አበባ የጦር ሜዳ አድርጎ የሚያወሩ አሉ፣ ስለዚህ ጉዳይ እኛ ካልተናገርን ማነው የሚናገርልን?

መስተንግዶ:- የቱሪዝም መሰረተ ልማትን ከሟሟላት አንጻር በመንግስት እየተሰሩ ያሉ ሥራዎችና ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት ቅድም ከገለጹት የመሰረተ ልማት እጥረት በማነጻጸር እንዴት ያዩታል?

ወ/ሮ ሳምራዊት:-በሀገር ደረጃ በመንግስት የተሰሩ ሎጆችና ሪዞርቶች፣ መሰረተ ልማቶችን ለማንሳት የቱሪስት አይነቱን ማየት ነው:: እኛ ከፍተኛ ወጪ አውጥቶ መጎብኘት የሚችሉ (High-end) ትላልቅ ቱሪስቶች አሉን? በመጠነኛ ደረጃ አሉ፣ የሚመጥናቸውን ሆቴል ፍለጋ በቻርተር ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ የሚያድሩ አሉ ግን በጣም ጥቂት ናቸው:: አሁን እየተሰሩያሉትን ስንመለከት ስለዋጋቸው ባላውቅም አንዳንድ ጊዜ ሂዶ ሥራውን ለማስተዋወቅም መታየት አለበት ብዬ አምናለሁ:: በሚዲያ ብቻ ይህ ተሰራ ተብሎ እናያለን፤ ሥራው ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ እና ያቀፈ ቢሆን ይመረጣል፤ ትልልቅ ሚዲያዎችን ተጠቅሞ ማስተዋወቅም ያስፈልጋል:: የተሰራው ሥራ በጣም ጥሩ ነው፣ ተደራሽነትን ለማምጣት ከባለድርሻ አካላት ጋር መስራት ደግሞ ያስፈልጋል:: አዲስ አበባ ውስጥ የተሰሩትን ለምሳሌ የአድዋ ፕሮጀክትን ብንወስድ የአፍሪካ ኩራት ነው፤ አፍሪካውያን ከኛ በላይ በድሉና በእኛ ኩራት አላቸው፣ ይህ ትልቅ ግብዓት ነው፣ በጣም ትልቅ ሥራ ነው የተሰራው መሸጥ መተዋወቅ አለበት::

የመሰረተ ልማት በተለይ የመንገድ ጉዳይ በደንብ ትኩረት ይፈልጋል፤ ለምሳሌ ባሌ ብዙ የቱሪስት መስህብ አለ፣ ከዱር እንስሳት ጋር ትስስር ያላቸው ጎብኝዎች መሄድ ይፈልጋሉ፣ የማደሪያ ቦታ የለም ይህን በትኩረት ይሻል፤ ይህን ለማስተካከል የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብት ማሰራት ይቻላል::

መስተንግዶ:- የዓለም አቀፍ ሁኔታን በሚመለከት

ወ/ሮ ሳምራዊት:- ኮቪድ ንጽህና እና መጎብኘትን አስተማረን:: ከኮቪድ በኋላ ሰው መጎብኘት ይፈልጋል፣ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተንቀሳቅሶ ማየት ይፈልጋል:: ሰው ቤቱ ቁጭ ባለበት ወቅት በቨርቹዋል ሪያሊቲ የተለያዩ ቦታዎችን እየጎበኘን ነበር:: ከአፍሪካ ሀገራት እነ ሩዋንዳ፣ ኬንያና የመሳሰሉት በዘርፉ የተሻለ እየሰሩ ይገኛሉ:: በዓለም ገጽታ ውስጥ እራሳቸውን በሚገባ ስለሸጡ ኬንያ መሄድን ይመርጣል:: የኬንያ ቱሪዝም ቦርድ የትኛውም ሀገር ላይ ተወካይ አለው፣ ተደራሽነታቸውም ከፍ ያለ ነው:: ይህ በኢንቨስትመንትም ጭምር ተደራሽ አድርጓቸዋል:: ለምሳሌ እስራኤል ላይ ጦርነት አለ ነገር ግን ለትንሳኤ በዓል ጉብኝት የሚሄዱ አማኞች ጉዞ አልተቋረጠም::

ምንም ያህል ጦርነት ቢኖር መንግስት የሚያደርገው ጥበቃና ራሳቸውን ለመሸጥ በሚያደረጉት ጥረት ምናልባት የጎብኚ ቁጥር ሊቀንስ ይችል ይሆናል እንጂ አትሂዱ የሚል ክልከላ አንሰማም::

ዓለም ላይ ቀውስ (crisis) አለ ግን የቱሪዝም ዘርፉ አልቀነሰም፤ ሌላው ዓለም ላይ እየተሰራ ነው በተለይ ማህበራዊ ሚዲያውን በመጠቀም ላይ ከቴክኖሎጂው ጋር መሄድ አለብን፡፡

መስተንግዶ፡-የቱሪዝም ኢንደስትሪ ለሴቶች ሰፊ የሥራ እድል የፈጥራል ይባላል እውነት ይሆን? እርስዎ ሴት ኖዎት ከዚህ አባባል ጋር በተያያዘ ምን ይላሉ ? ምንስ ገጠመኝ አሎዎት፣ ዘርፉ ላይ ከሴቶች ጋር በተያያዘ እየሰሩት ያለው ሥራ ካለ?

ወ/ሮ ሳምራዊት፡- እኔ ብሔራዊ አስጎብኝ ድርጅት በነበርኩበት ወቅት ሴት አስጎብኚዎች ነበሩ፡፡ ግን በዚያን ጊዜ እነዚህ ሴት አስጎብኝዎች መስራት አልቻሉም፤ ምክኒያቱም በወቅቱ የነበረው ንቃተ ህሊና አሁን እንዳለው አልነበረም፡፡ ሴቶቹን ከውጭ ሀገር ዜጎች ጋር ሲያዩዋቸው ሌላ ስም ይሰጧቸዋል፣ እንግዶችን አስጎብኝተው ሆቴላቸው በሚያድሩበት ወቅት ችግር ይደርስባቸው ነበር፡፡ መጨረሻ ስላልቻሉ ይቅርብኝ ብለው የቢሮ ሰራተኛ የሆኑ አሉ፡፡ የኛ ድርጅት 1994 ሲጀምር ድርጅታችን ሴት አስጎብኚዎችን ሲቀጥር የመጀመሪያው ነው፤ አሁንም አብዛኛው ሰራተኞቻችን ሴቶች ናቸው፡፡

አስጎብኝነት ሴቶችን ልዩ የሚያደርገው አብዛኛው ቱሪስት መጥቶ የሚጠይቀው ስለ አኗኗር፣ ባህል፣ጋብቻ፣ የሴቶች ድርሻ(ተሳትፎ)፣ በሀገራችን ምንያህል ተቀባይነት አላቸው የሚለውን ነው፤ ስለማህበረሰቡ ከሴቶች በላይ የሚናገር የለም፡፡ ሴት የሚሰጣትን ሥራ ከብዙ አቅጣጫ አይታ ነው የምታከናው ነው፡፡ የኛ ስራ ደግሞ እዚህ ላይ ተሳሳትኩ ብሎ ነገር የለም፤ መሳሳት ብዙ ዋጋ ያስከፍላል፡፡ ስለዚህ ሴት ተጠንቅቃ ነው የምትሰራው፣ ውጤታማም ናቸው፡፡ ሃሳብን በመግለጽ እና በማስረዳት ላይ የደምበኞችን ፍላጎት ተረድታ ገለጻ ታደርጋለች የአስጎብኝ ሴቶች ብቃት ያስደንቃል፡፡

ከሥራ ፈጠራ አንጻር የቡና ጠጡ ሥራዎችን፣ የእደ ጥበብ ሽያጭ ስናይ ተጠቃሚዎች ሴቶች ናቸው፡፡ የሀገር ባህል ልብስ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዴት እንደ ተለወጠ ማየት ይቻላል፤ በዘርፉ ውስጥ ብዙ የሴት ተሳትፎ አለ፤ በየአካባቢው ቱሪዝም ለሴቶች ሰፊ የሥራ እድል ይፈጥራል፡፡ ከዚህ ጋር በተያይዘ በቱሪስት መዳረሻ አካባቢዎች ላይ በቂ የስጦታ እቃዎች መሸጫ ስለሌለ ሴቶች ተጠቃሚ እየሆኑ አይደለም ፤ ያለንን ሃብትም በሚገባ እየተጠቀምንበት አይደለም፤ ሴቶች በዚህ ዘርፍ ቢሳተፉ የተሻለ የሥራ እድል ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ፡፡ የሀገራችን ሴቶች አንዴ መንገድ ብናሳያቸው እራሳቸውን ማውጣት ይችላሉ፤ በስነልቦና እና በአቅም ማብቃት ያስፈልጋል፡፡ በየአካባቢው የእደ ጥበብ ስራዎች፣ ባህላዊ ክንዋኔዎችን ብናቀርብ የተሻለ የሥራ እድል ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ፡፡ ቱሪዝም ለወጣቶች ሰፊ የሥራ እድል የሚፈጥር ዘርፍ ነው፣ ለዚህ ደግሞ ከባለድርሻ አካላትም ጋር በቅርበት መስራት ያስፈልጋል፡፡

መስተንግዶ፡- የመሰናበቻ መልዕክትዎ ?

ወ/ሮ ሳምራዊት፡- እኔ ያለኝ መልዕክት በጣም ብቃት ያላቸው መምህራንን በመጠቀም በጣም ብቃት ያላቸውን አስጎብኝዎች፣ የቢሮ ሰራተኞችና እናውጣ፡፡ ይህ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ለቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ብቻ የተሰጠ ኃላፊነት ሳይሆን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የሚሰራ ነው፡፡

ለምሳሌ አዳዲስ አስጎብኚዎችን አሰልጥኖ ካበቁ በኋላ አንዱ ድርጅት መጥቶ ይወስዳል፤ የባለሙያ መቀማማት ይታያል፡፡ ይህ በኢንዱስትሪው ውስጥ የሰለጠነ የሰው ሀይል እጥረት መኖሩን ያሳያል፡፡ ይሄን ለመቅረፍ ከሆቴሎች፣ ቱር ኦፕሬተሮች ጋር መነጋገር፣ ኢንስቲትዩቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀራርቦ መስራት ይገባል፡፡

መስተንግዶ፡- ለሰጡን ጊዜ ከልብ እናመሰግናለን፡፡

ወ/ሮ ሳምራዊት፡- እኔም ለተሰጠኝ እድል በጣም አመሰግናለሁ ፡፡



# የጉዞ ማስታዎሻ

ወደዚህም ተመልከቱ፤ አስደናቂው እና ያልተነገረለት የቱሪዝም ጉዞ መስመር
በተጓዡ ጋዜጠኛ ሄኖክ ስዩም

ሄኖክ ስዩም የጉዞና ጉብኝት ጋዜጠኛ ነው:: የሀገሬ ሚዲያ መስራችና ሥራ አስኪያጅ ሲሆን ጉዞ ኢትዮጵያ የተባለ ሳምንታዊ የቴሌቭዥን ፕሮግራም እያዘጋጀ በኤን ቢ ሲ ቴሌቭዥን አየር ላይ ያውላል:: በህትመት፣ በዲጂታል እና በሬዲዮ ተከታታይ የጉዞ ማስታወሻ ዘገባዎችን ይሰራል: : አራት የጉዞ ማስታወሻ መጽሐፍትም አሉት:: በዚህ ዕትም “ወደዚህም ተመልከቱ” ሲል አዲስ የቱሪዝም መስመርን ያስተዋውቀናል::

እንደ ጉዞ ጋዜጠኛ ሰዎች ሁሉ ወደዚህ አዲስ መስመር ይጓዙ ዘንድ እመክራለሁ። ይህ በኢትዮጵያ የቱሪዝም ቀጠና ውስጥ ቦታም ስምም የሌለው የጉዞ መስመር /ltnery/ ነው።

ከአዲስ አበባ ለሚነሱ ጎብኚዎች ብዙ አማራጭ መንገድ አለው። አንደኛው የተለመደውን የስምጥ ሸለቆ መስመር ተከትሎ ወላይታ ሶዶ ድረስ መጓዝ ነው። የተለመደውን ልበል እንጂ ባልተለመዱ መዳረሻዎች /unusual tourism routes/ የተለየ ጊዜን ስለማሳለፍ ልጠቁማችሁ እወዳለሁ።

አንዱ የባቱ ከተማ የወይን ቱሪዝም /wine tour-ism/ ጉብኝት ነው። ባቱ አሁን ለቱሪስት የበለጠ ምቹ ሆናለች። Enotourism በዓለም ላይ ወይንን ከቱሪዝም ያዛመደ ፍልስፍና ሲሆን በኢትዮጵያ ዝዋይ ወይም ባቱ አሁን አብዮቱ ፈንድቷል: : በባቱ የወይን ቱሪዝም /wine tourism/ እና በቡልቡላ የግብርና ጉብኝት /agrotourism/ የተባሉ ሁለት የመዳረሻ ቦታዎች በኦሮሚያ ቱሪዝም አማካኝነት ለገበያ ቀርበዋል። ሀሮ ደንበል ሐይቅ ላይ ቆይታ ማድረግ ለሚሹ ወደ ታሪካዊ ደሴቶች ተጉዞ መጎብኘት ቀላል ሆኗል። በአቢጃታ ሻላ እንደ ላንጋኖ ሁሉ ጥሩ ጊዜ ማሳለፍ ይቻላል። በተለይም የሻላ ሐይቅ ዳርቻ አሁን ለካምፕ ሳይት ምቹ ተደርጓል። በኢኮ ቱሪዝም ማኅበር የተሰራም ሎጂ አለው። ከምንም በላይ ላበስራችሁ የምፈልገው በሻላ ላይ መጓዝ የምትችሉ መሆኑን ነው።

በኢትዮጵያ በጥልቀቱ አንደኛ የሆነው ሻላ 266 ሜትር ድረስ ይጠልቃል። እንግዲህ በጥልቁ ሐይቅ ላይ ስትንሸራሸሩ አስቡት። ሐይቁ ለረዥም ዘመን የቱሪስት ጀልባ አልነበረውም። በዚህ ምክንያት የሻላ ደሴቶች ለጉብኚ ብርቅ ሆነው ኖረዋል። አሁን ያ ዘመን ማብቃቱን እነግራችኋለሁ። ጥሩ ምሽት በሻላ ዳርቻ አሳልፋችሁ፣ በፈዋሹ ፍል ውሃ ታጥባችሁ፣ የአእዋፍ ዓለም ወደ ሆኑ የሻላ ደሴቶች መጓዝ እጅግ ቀላል ሆኗል።
ሻሸመኔ የከተማ ቱሪዝም ምርጫቸው ለሆነ ሰዎች ስንዱ ናት። ወደ ወንዶ ገነት ጎራ ማለት ቀላል መሆኑም ቀጠናውን ተመራጭ ያደርገዋል።
ሌላው ከሻሸመኔ ሀላባ መካከል ጎራ የምትሉበት

ያልተለመደ የጎብኚ መዳረሻ ስንቀሌ ቆርኪዎች መጠለያ ነው። በኢትዮጵያ ብርቅዬውን የስዋይን ቆርኪ ትመለከቱበታላችሁ። በቆርኪ ይታወቅ እንጂ የሜዳ ፍየሉ ብዙ ነው። በቀላሉ ብዙ ዱር እንስሳት ትመለከታላችሁ። የእግር ጉዞ ለሚወዱ ተራራ አፍቃሪያን ደግሞ ላሊማ አለ። ትልቁ የመጠለያው ተራራ ሲሆን በምሽት ሀዋሳ ከተማን ፍንትው አድርጎ ያሳያል። ከስንቀሌ የወጣ ሰው ሀላባ ሲደርስ ቁሊቶ ማረፍ አለበት። ሀላባ ብቻውን የሚያስነብት ብዙ ባህላዊ እሴቶችን የያዘ ምድር ነው። ስትሄዱ ስለምታዩት ነገር እየጠቆምኩ ልለፍ። እስከ ወላይታ።

እኔ ብዙ ጊዜ የምጓዝበት ሌላኛውን መስመር ነው። አሁን ሂዱበት የምላችሁ ቀጠና የኢትዮጵያ ቱሪዝም አልሄደበትም። ከሄደም አዳዲ፣ መልከአ ቁንጥሬ እና ጢያ ጎራ ብሎ ያበቃል።

እርግጥ ነው አዳዲ በጣም ጥንታዊና በዘመነ ዛጉዌ የተሰራች ዋሻ ቤተ ክርስቲያን ናት። ለአዲስ አበባ ቅርብ ሆና ለቱሪዝም መራቋ ያስቆጨኛል። መልከአ ቁንጥሬ ደግሞ ብዙ ጎብኚዎች የሚዘሉት ግን ደግሞ በሰው ልጅ የስልጣኔ ታሪክ ውስጥ ትርጉም ያለው የአርኪኦሎጂ ስፍራ እንደሆነ ተረጋግጧል። Open Air Museum የሚለውን አይቼበታለሁ። የሰው ልጅ አድኖ የበላበትን ዘመን ታሪክ ከነ አደን ቁሳቁሱ የተመለከትኩበት የአዋሽ ወንዝ ዳርቻ ነው። ድንኳን ጥለው ለሚያርፍ የተመቸ ቅጥር አለው። በስፍራው የተገኙ የአርኪኦሎጂ ግኝቶችን የያዘ ቤተ መዘክሩን ደጋግሜ ጎብኝቼዋለሁ።

የታወቀ ነውና ስለ ጢያ ብዙ ማለት የለብኝም። የዓለም ቅርሱን የትክል ድንጋይ መካነ ቅርስ ስለምትጎበኙበት መስመር ድብቅ ፀጋዎች ላጋራችሁ።

> ... በቀጥታ ከጩርጩራ ቀጠና ወደ ጨበራ ትመጣላችሁ። እነ ቡሎ ሐይቅ በቀላሉ...

ምድረ ከብድ ጥንታዊ ገዳም ነው። ከዝቋላ ጋር ይገናኛል። መስራቹም እራሳቸው አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ናቸው። የዓለም ገና ቡታጅራ መስመር ይሄንን ገዳም ለመጎብኘት ዕድል ይሰጣል።

ተፈጥሮ የሚወዱት የማያልፉት የዘቢዳርን ዙሪያ ገባ ነው። የዳሙ ገነት መልከአ ምድር እጅግ ይለያል። ወገራም አስደናቂ የዕይታ ማማዎች ይገኙበታል። በተለይም Nature Addicts ለሚባሉ የተፈጥሮ ጉብኝት ሱሰኞችና የተራራ ተጓዦች /Mountainers/ ከሐምሌ እስከ ጥቅምት ከመጡ እንደ እኔ በሶዶ ተፈጥሮ ተይዘው ይቀራሉ። መስከረምን ለሚያስቡ ጎብኚዎች መስቀል ከመጡ አከባበሩ ይለያል። በመስከረም ሌላው የሶዶ ኩነት አዳብና ነው።

ቡታጅራ እንዲሁ አትታለፍም። እኔ የክትፎዋ ሱሰኛ ነኝ። የምግብ ቱሪዝም ተጓዦች የቡታጅራ ቆይታቸውን እንደሚወዱት አልጠራጠርም። ከቡታጅራ ወደ ወራቤ በሚወስደው መንገድ ዘጠኝ ኪሎ ሜትር ተጉዘው የሚያገኙት ባለ ቀለም ሐይቅ ነው። ደጋግሜ ሄጄበታለሁ፣ አፋፍ ላይ አድሬያለሁ፣ በወገቡ ዱር ውስጥ ተጉዣለሁ። ልነግራችሁ የምችለው በጣም የምትወዱት ስፍራ ተደብቆ መኖሩን ነው።

ሐይቁ 17 ሄክታር ገደማ በሚጠጋ መሬት ላይ አርፏል። ከአፋፉ እስከ ሐይቁ ያለው ርቀት 260 ሜትር ይደርሳል። ወደ ሐይቁ ለመውረድ የሚታለፍበት መንገድ በደን ተሸፍኗል። የአካባቢው ሰዎች ድንጋይ አንስተው ከሐይቁ አፋፍ በመወርወር ወደ ሐይቁ አድርሱት ካሏችሁ ሞክሩ። አታሳኩትም፤ ግን ማን ያውቃል?

ሐይቁ አፋፍ ለምታድሩ ጎብኚዎች እኔ

ያጣጣምኩትን ደስ የሚል የምሽት ሕይወት ታጣጥሙታላችሁ። የአካባቢው ወጣቶች የምትፈልጉትን ያግዟችኋል። ሲመሽ ጅብ እንደ ልብ ታያላችሁ። ጨረቃ ሀረ ሸይጣን አናት ስትሆን ውበቱ አይፃፍም።
ሲነጋ አይናጌ ዋሻን ታያላችሁ። ወደ አይናጌ ስሄድ በሁለት ነገር እገረማለሁ። በዋሻውና በዋሻው ውስጥ ነዋሪ ቤተሰቦች።
ስልጤ በሐይቅ ሀብት ታድሏል። ሀረ ሸይጣን አቅራቢያ ከቅበት በስተምስራቅ 10 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ምስራቅ ስልጤ ወረዳ ገርቢበር የሚገኝ ሐይቅ ነው። አበያ ስልጤ ሐይቅ 1500 ሄክታር መሬት ያረፈና ለጎብኚ በጣም የተመቸ ነው። ስትደርሱ እኔ ያልኩትን ትላላችሁ፤ "እስከ ዛሬ የት ነበር?" የሐይቁ ዳርቻ ለማደር ምቹ የሚለው ቃል አይገልፀውም። ስልጤ ሰላማዊ ምድር ነው። ሌሊቱ ደስ የሚል ስሜት ፈጥሮብኝ ነበር። የጅቦች ድምፅ ሰማሁ፤ ቀበሮ ሳደምጥ አደርኩ።
ጉማሬ ማየት ትፈልጋላችሁ? አበያ ስልጤ ምቹ ሐይቅ ነው። በአግኖቴ ተሳፍሬ ወደ ሌላው የሐይቁ ዳርቻ ተጓዝኩ። አግኖቴ የጀልባዋ ስም ሲሆን በስልጥኛ በኩር ወይም የመጀመሪያ የሚል ትርጉም አለው። ከዚያ ወደ ጉማሬ በር ተጓዝን፤ ወደ አንዱ የሐይቁ ዳርቻ በዚያ ያየሁት ጉማሬ እና ወፍ አፈዘዘኝ።

የሻሞሮ ተራራን እያዩ፣ ዳክዬዎቹ ሲቀዝፉ፣ አባ ኮዳው አሳ ሲያስስ ትመለከታላችሁ። ለወፍ ቱሪዝም /Birdwatching/ የተመቸ ቦታ ነው።
የአበያ ስልጤ ሐይቅ ጉብኝታችሁን ስትጨርሱ ወደ ለሞሬ ፏፏቴ ውሰዱን በሏቸው። ስለማትጠብቁት በምታዩት ነገር ትፈዛላችሁ። ለሞሬ ፏፏቴ ጓሮሬና ለቦ የሚባሉ ሁለት ወንዞች የፈጠሩት ሲሆን ወንዞቹ ይገናኙና ከከፍተኛ ቦታ ወርደው የሚያምር ፏፏቴ ይፈጥራሉ።
ወራቤ የስልጤ መዲና ናት። ለሀላል ቱሪዝም ተጓዦች ለምርጫ ወደር የላትም። ወደ ስልጤ ምድር የሚመጡ ጎብኚዎች አረፋ ሲከበር ቢደርሱ "እስከ ዛሬ በገዛ ሀገሬ ስንቱ አምልጦኝ የለ?" እንደሚሉ አልጠራጠርም። ብዙ ጊዜ ከስልጤ ጋር አረፋን ሳከብር ደጋግሜ ያልኩት ይሄንኑ ነበርና።

ወደ ሆሳዕና ስትመጡ የጉብኝት ፕሮግራማችሁ ላይ ማካተት ያለባችሁ የሃይቅ ጉብኝት ነው። ሌላ ልዩ የመዝናኛ ዳርቻ ያለው ሐይቅ ልጠቁማችሁ ቡድ አመዳ ይባላል። በሀዲያ ዞን ሲራሮ ባደዋቾ ወረዳ ከሆሳዕና ከተማ በ120 ከአዲስ አበባ ደግሞ 340 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል።
በእዚያው መጨፈራ ሐይቅን መጎብኘት ትችላላችሁ። ጉማሬ እና አዞ ማየት ለሚወዱ ጎብኚዎች ተመራጭ ነው። ከሆሳዕና 110 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በተመሳሳይ ወረዳ ውስጥ ይገኛል። ሐይቁ 145 ሄክታር የሚሆን ቦታ ላይ ያረፈ ነው። ወደ ሃድያ ጎራ የሚሉ ሰዎች በመስከረም አጋማሽ ከደረሱ ያሆዴን የመመልከት ዕድል ይኖራቸዋል። ያ ሆዴ የሃድያ ዘመን መለወጫ በዓል ነው።
ሌላው አሁን ገናና እየሆነ የመጣው የዚህ መስመር የተፈጥሮ መዳረሻ ሀምበርቾ ይባላል። የከንባታዎች መዲና በሆነችው ዱራሜ አጠገብ የሚገኘው ሀምበርቾ 777 የደረጃ መወጣጫ ያለው ለተራራ ቱሪዝም የተመቸ ድንቅ ስፍራ ነው።
ከባህር ጠለል በላይ 3056 ሜትር ከፍታ ያለው ሀምበርቾ በተራራ ቱሪዝም ተጓዦች በጣም ተወደደል። በ'ሌላ በኩል በከንባታ ጠንባሮ በኩል አጀራ መንትያ ፏፏቴን መመልከት ለምትፈልጉ በጉዞ መስመራችሁ ላዩ የሚገኘውን ገመሻ ጎራ በሉበት። ፈዋሽ የተፈጥሮ ፍልውሃ ነው። ከዚያ እዛው ቅጥር ጊቢ የሚገኘው አስደናቂ ዛፍ ጠይቃችሁ ተመልከቱት። ሰባት የዛፍ ዝርያዎችን በአንድ ላይ የያዘ ዛፍ።
ወላይታ ሶዶ ብዙዎች በጥሬ ስጋዋ ያውቋታል። ሶዶ ግን የምታከርም የቱሪዝም ከተማ ናት። እኔ ወደ ቀጣዩ ጉዟችን ከመሄዳችን በፊት ዳሞትን ጎብኙ እላለሁ።
ዳሞታ ተራራ ከባህር ወለል በላይ 3000

ሜትር ይረዝማል። መጠነ ዙሪያው ደግሞ 68 ኪሎ ሜትር ገደማ ይሸፍናል፡፡ ዳሞታ ተራራ ብቻ አይደለም። ታሪካዊ ቅርሶች፣ ሀገር በቀል እፅዋትና ዱር እንስሳትን ጨምሮ በርካታ መስህቦች ይገኙበታል። በጥንታዊ የወላይታ ነገሥታት መናገሻነት የሚታወቁ ስፍራዎችንም ይዟል፡፡ ወላይታዎች ጣዛ ገሮ (Xaazaa Garo) የሚሏቸውን ታሪካዊ ስፍራዎች የያዘው ተራራ በተፈጥሮ ውበትና ሀብት የታደለ ነው፡፡

ዳሞታ ከአቡነ ተክለሃይማኖት ጋር ይገናኛል፤ አቡነ ተክለሃይማኖት ክርስትናን ለመስበክ በተራራው አናት በሚንቀሳቀሱበት ወቅት በሚመላለሱበት መንገድ ላይ የሚገኝና ዘወትር ሲደክማቸው አረፍ የሚሉበት እንደሆነ ይታመናል፡፡ ያኔ ሀገሬው ጦሳ ፔንጊያ ሲሉ የእግዜር መተላለፊያ በሚል ሰየመው፡፡
ከገናናው የወላይታ ስርወ መንግስት ከብርቱዎቹ የጦር ጀግኖችና ካልተነገረለት አያሌ ታሪክ ጋር ይቆራኛሉ፡፡ ዳሞታ የመሬት ብቻ ሳይሆን የወላይታዎች የባህል ከፍታ ማሳያ ነው፡፡
ከዚያ ጉዞው ወደ ዳውሮ ምድር ይቀጥላል። በቀጥታ ታርጫ ትገባላችሁ። ግን እንደ እኔ በየመንገዱ ቁሙ። ለምሳሌ በጊቤ ሦስት የኃይል ማመንጫ አማካኝነት የተፈጠረውን ሰው ሰራሽ ሐይቅ ቆም እያሉ መመልከት ልዩ ስሜት ይፈጥራል።
በተለይ ሀላላ ኬላን አለማየት የመቅረት ያኽል ነው። የንጉሥ ሀላላ ድንጋይ ካብ (ሀላላ ኬላ) ዳውሮን ከውጪ ወራሪ ኃይል ፈረሰኛና እግረኛ ጦር ለመከላከል የተገነባ እንደኾነ ታሪኩ ይነገራል።

የጎፋ ዞን ማሎ ኮዛ ወሰን ጀምሮ ኦሞ ወንዝን ተከትሎ በዳውሮ ምድር የተገነባው (Kawo Halalaa Keelaa) የካዎ ሀላላ ድንጋይ ካብ (ኬላ) ኢሠራ፣ ዲሳ፣ ሎማ፣ ዛባ ጋዞ፣ ጌና፣ ታርጫ ከተማ አስተዳደር እና ታርጫ ዙሪያ የሚገኙ የዳውሮ ወረዳዎችን ያካልላል። ወላይታ፣ ከምባታ ጠንባሮ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጅማ እና ወደ ኮንታ ዞኖች መሻገሪያ ድንበሮችን ያካለለ ታሪካዊ የኪነ-ሕንፃ ግንባታ ነው።
ከ15ኛው እስከ 18ኛው ክፍለ ዘመን የዳውሮ ህዝብን ያስተዳድሩ የነበሩ 14 ነገሥታት በቅብብሎሽ የገነቡት ይህ የ"ሀላላ" ካብ በ1532 ዓ.ም.ግንባታው ቢጀመርም ከ1782 እስከ1822 ዓ.ም. ዳውሮን በንጉሥነት ይመሩ የነበሩት ንጉሥ ሀላላ ስላስጨረሱት በስማቸው ሊጠራ ችሏል።

በአንድ ረድፍ 175 ኪሎ ሜትሮችን የሚረዝመው የሀላላ ድንጋይ ካብ በሰባት ረድፍ ያለው አጠቃለይ ርዝመቱ 1225 ኪሎ ሜትር ይሸፍናል። ከ2.5 እስከ 5 ሜትር ስፋትና ከ2.5 እስከ 3.8 ሜትር ከፍታ አለው።
ሀላላ የደረሰ ጎራ ሊልበት የሚገባው ሌላ መስህብ በጊቤ ሦስት የኃይል ማመንጫ አማካኝነት ከተፈጠረው ሰው ሰራሽ ሐይቅ ዳርቻ የሚገኘውና በ'ገበታ ለሀገር' ኮይሻ ኮሪደር ፕሮጀክት የለማው ሀላላ ኬላ ሪዞርት ነው።
አሁን ወደ አፍሪካ ዝኖኖች ዓለም እንጓዝ። ጨበራ ጨርጨራ ብሔራዊ ፓርክን እንጎበኛለን። የምንገባው በዳውሮ ደጋ ምድር ነው። በኢሠራ ወደ ጉድሙ።

የብሔራዊ ፓርኩን ከፍተኛ ቦታ የምትጎበኙበት ቀጠና በጉም የሚሸፈኑ ተራሮች ሞልተውበታል። ወደ ፓርኩ ስትገቡ ከአፍሪካ ዝኖኖች ጋር ትገናኛላችሁ። አዳራችሁ ጨፎሮ ሐይቅ አፋፍ እንዲሆን እጠቁማለሁ። በዚያ በነበሩኝ አዳሮች በርካታ ጉማሬ እንደልብ አይቻለሁ። ጎሽ ይርመሰመስበታል።
በፓርኩ ውስጥ በቀጥታ ከጨርጨራ ቀጠና ወደ ጨበራ ትመጣላችሁ። እነ ቡሎ ሐይቅ በቀላሉ ይጎበኛሉ። የእግር ጉዞ የሚወዱ ጎብኚዎች ባሂ ወደተባለው ሐይቅ ሄደው በዳርቻው ካምፕ ቢያደርጉ "ኢትዮጵያማ ታድላለች" ማለታቸው አይቀርም።

ጨበራ ጩርጩራ የሐይቆች ባለፀጋ ነው። ከረቤላ በቀላሉ ይገኛል። ሺታ ወደሚባለው ሐይቅ ለመጓዝ የመንገዱ ውበትና የኮንታ ገጠሮች እንግዳ ተቀባይነት ጉልበት ይሆናል። ጎሽና ዝኆን አለ ድካም ትመለከታላችሁ። ጨበራ የዝኆን ዳና ሎጅም አለ። አመያ ቆይታችሁ መልሳችሁ በጅማ ይሆናል።

ስለ ጅማ የቱ ተነግሮ የቱ ይቀራል? ለከተማ ቱሪዝም ምቹ ናት። የአዌቱ ወንዝ ዳርቻዎች ለምተዋል። ፈረንጅ አራዳ ጥሩ ጥሩ ጊዜ ለማሳለፍ ተመራጭ ነው። ጅማ ሙዚየምን ሳትጎበኙ እንዳትመለሱ። እዚያ ከደረሳችሁ ጅሬን ለመጓዝ ትነሳሳላችሁ።

ጅሬን የጅማ የቀድሞ ከተማ ስትሆን የአባ ጅፋር ቤተ መንግሥት ይገኝባታል። የነገሥታቱ ታሪክ ከነ ቅርሱ በዚያ ከፍታ ላይ ይገኛል።

የቻለ በካፋ ሚዛን ቢገባ አልያም በአጋሮ ጋምቤላ ሌላ አዲስ ዓለም ይተዋወቃል። በተለይ ኢሉ አባ ቦራ ኢኮ ቱሪዝም ቀጠናና የሸካ ጥብቅ ደን እስከ ማጃንግ ገና አልተነገረላቸውም። ከማንኪራ እስከ ኦሞ ፓርክ በቱሪዝም ገበያ ውስጥ ያልተሸጠ ቀጠና እንደሆነ ይሰማኛል።

በየመንገዱ መቆም በየመንገዱ ማደር ትችላላችሁ። እንዲህ የማሮጣችሁ ብንቆምም የማንጨርሰው ቀጠና ስለመጣን ነው።

ሳጃ ጎራ እንላለን። የየም ዞን ዋና ከተማዋ ሳጃ በርካታ ቅርስ ከቧታል። ወደ አንጋሪ ቤተ መንግሥት ተጓዙ። ፎፋ መድኃኒዓለምን ትጎበኛላችሁ። የየም መልከአ ምድር ዓይን ያፈዛል። የሶፍካር ትክል ድንጋይ የሚባል በቀላሉ ታያላችሁ። ወደ የም መስከረም ሦስተኛ ሳምንት ከደረሳችሁ ሄቦ በዓል የማየት ዕድል አላችሁ። ሄቦ የየም ዘመን መለወጫ ነው። እኔ ከየም ጋር ሄቦንም ቻሎንም የማየት እድል ደጋግሜ ስላገኘሁ ምስክርነቴን ተቀበሉት። መስከረም አልፏችሁ ጥቅምት አጋማሽ የምትደርሱ ቦር የሚባል የፈውስ ተራራቸው ላይ የሞች የመድኃኒት ለቀማ ሥርዓት ሲያከናውኑ አብሮ የመሆን አጋጣሚ አገኛችሁ ማለት ነው።

አበልቲ ዶሮ አርስቶን ሳይቀምሱ መመለስ ልክ አይደለም። ከዚያ ጊቤ ሸለቆ ብሔራዊ ፓርክ ጎራ ይባላል። ፓርኩ በጉራጌ ዞን ለአዲስ አበባ 178 ኪሎ ሜትር ሲቀራችሁ የጊቤ ወንዝን ተከትሎ ያረፈ ነው። ከ30 በላይ የፍል ውኃ ምንጮች አሉት። ገናናው ሉቄ ፍል ውኃ ይባላል።

አንበሳ፣ አጋዘን፣ ድኩላ፣ ዘንዶ፣ ነብር፣ ከርከሮ፣ የዱር አሳማ፣ ዝንጀሮ፣ ጦጣ፣ ጉሬዛ፣ ፌቆ፣ አዞ፣ ሽኮኮ፣ አልድጌሻ፣ ዱፋርሳና የመሳሰሉ የዱር እንስሳትን ማየት የሚችሉበት ፓርክ ነው። በጉማሬ ብዛቱ ይታወቃል። ከዚያ 20 ኪሎ ሜትር ተጉዘው ወልቂጤ ይገባሉ።

ወልቂጤ የባህልና የተፈጥሮ ቅርሶች መዲና ናት። በአንድ ቀን አዳር እንደ ዘቢሞላና ቃጥበሬ ያሉ ታሪካዊ መስጂዶችን ጎብኝቶ የመመለስ ዕድል ትፈጥራለች። እንደ እኔ ሀሳብ ያየሁትን ትመለከቱ ዘንድ ረመዳን እዚህ ብትደርሱ ሌላ ተአምር ታያላችሁ። ወልቂጤ የክትፎ መዲና መሆኗን መጠቆም ያስፈልጋል።

ከወልቂጤ በወሊሶ ወደ አዲስ አበባ እንዲሁ አይመጣም። ወሊሶ ነጋሽ ልጇስ? ፍል ውሃው መድኃኒት ነው።

ከወሊሶ በተፍኪ ለሚመጡ ሰዎች መናገሻ ሱባ ጎራ አለማለት የበይ ተመልካችነት ይመስለኛል። ከወሊሶ በወንጪ አምቦ ገብተን እንመለሳለን ለሚሉ ደግሞ መቼም ወንጪ የሚኖራቸውን ቆይታ መገመት ነው።

ይሄንን የጎብኚ መስመር የኢትዮጵያ ቱሪዝም ስም እስኪያወጣለት እኔ ድብቁ ቀጠና ብዬዋለሁ። ተፈጥሮ አለው፣ የነገሥታት ታሪክ ሞልቶበታል፣ ባህል ይታይበታል፣ ለከተማ ቱሪዝም የተመቹ ከተሞች ብዙ ናቸው። ከ3000 በላይ የሆኑ ተራሮች ሞልተውታል። ብሔራዊ ፓርኮቹን ቁጠሯቸው! ለወንዝ ቱሪዝም ታድሏል። ምን የሌለው አለ?

# ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በ1961 ዓ.ም. መጨረሻ የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በሚል ስያሜ በእስራኤዊው ሚስተር ዲቪድ ኤፍራት ዳይሬክተርነት ሌሎች እስራኤላዊያን ኤክስፐርቶችን ጨምረው በእንግዳ አቀባበል፣ በቤት አያያዝና በምግብና መጠጥ መስተንግዶ መሠረታዊ የአንድ ዓመት ሥልጠና መስጠት መጀመሩን የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ፡፡

በወቅቱ በየሆቴሎቹ ያሉትን ሠራተኞች የአጫጭር ጊዜ የሙያ ሥልጠና መስጠት፣ ታክሲ ነጂዎች እንግዶቹን ሲያስተናግዱ የቋንቋ ችሎታቸውን በማሻሻል ተገቢውን የእንግዳ እንክብካቤ እንዲያውቁ ሥልጠናዎችን ይሰጥ ነበር፣ እንዲሁም ወጣት ተማሪዎችን በመደበኛ ፕሮግራም በማሰልጠን የቱሪስት አገልግሎቱን ለማሟላት ጥረት አድርጓል፡፡በሆቴልና ቱሪዝም ዙሪያ የማያቋርጥ ጥናት ማካሄድም አንዱ የዓላማው ነበር፡፡ተቋሙ ከጊዜ ወደ ጊዜ አቅሙን በማሳደግ በሙያው መምህራን እንዲገነባ ከመደረጉም በላይ ቀጣይነት ባለው የከፍተኛ ትምህርት ስልጠና መምህራን እውቀታቸውን እንዲያሳድጉም አድርጎ በርካታ የዘርፉ መምህራንና ባለሙያዎችን አፍርቷል፡፡
ኢንስቲትዩቱ በቱሪዝምና በሆቴል የሙያ ዘርፎች እስካሁን ከ30ሺህ በላይ የመደበኛና ተከታታይ ትምህርት ክፍል ያስመረቀ ሲሆን በየዓመቱ በሙያው ውስጠ ላሉ የሥራ ላይ ስልጠናም በልዩ ሁኔታ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

የተግባር ትምህርትን በተመለከተ የሆቴል ሰልጣኞች በተግባር በተቋሙ ከሚያገኙት ሥልጠና ባሻገር በከተማው የሚገኙ ባለኮከብ ሆቴሎች የትብብር ስልጠና ያገኛሉ፡፡ የቱሪዝም ሰልጣኞች በቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎቻችን በሶስት አቅጣጫ ሙሉ መዳረሻዎቻችን ከመምህራን ጋር በመጎብኘት የተግባር ሥልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም በአስጎብኚ ድርጅቶች አማካኝነት የትብብር ስልጠና ያገኛሉ፡፡

ተቋሙ በአሁኑ ጊዜ መንግስት ለዘርፉ የሰጠውን ልዩ ትኩረት መሰረት ያደረገ ስልጠና የሚሰጥባቸውን የሙያ መስኮች ደረጃ በማሳደግና በዘርፉ የልህቀት ማዕከል ለመሆን የሚያስችሉ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡
ሌላው በቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ኢንደስትሪውን በጥናትና ምርምር መደገፍ የሚያስችሉ ሥራዎች ትኩረት ተሰጥቶ እየሰራ ሲሆን በጥናትና ምርምር የሀገራችንን የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ባህላዊ ምግቦችን እያጠና በሆቴሎች የምግብ ዝርዝር ውስጥ እንዲገቡ እያደረገ ይገኛል፡፡
ከዩንቨርሲቲዎች ጋር በመተባበር የምርምር ኮንፈረንሶችን ያካሂዳል፡፡ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋርም የመግባቢያ ስምምነቶችን በመፈራረም በትብብር እየሰራ ይገኛል፡፡ በሀገር ውስጥም በዘርፉ ስልጠና የሚሰጡ የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆችን የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት እየተከናወኑ ካሉ ሥራዎቻችን የሚጠቀሱ ናቸው፡፡
መንግስት የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማትን በአንድ አደረጃጀት እንዲመሩ ለማድረግ ተጠሪነቱን ለሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አድርጎ በአዲስ መልክ ሲያደራጀው ቱሪዝም የዘርፉን የሰለጠነ የሰው ኃይል ልማት ላይ በሰፊው እንዲሰራ ከማቀድ አንጻር መሆኑ ዕሙን ነው፡፡
ስለሆነም በቱሪዝም ዘርፍ ሀገራችን ካላት

የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ መስህብ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርስ አንጻር ምንም ያልተሰራበት በመሆኑ ዘርፉን መደገፍና የሰለጠነና የበቃ የሰው ኃይል ማፍራት ልንመልሰው የሚገባን የወቅቱ ጥያቄ ነው፡፡

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በአሁኑ ጊዜ የመንግስት አስተዳደር ሪፎርም ሥርዓትን ተግባራዊ እያደረገ የሚገኝ ሲሆን ለሥራ አመቺ የሆኑ መመሪያዎችን እና የአሰራር ማዕቀፎችን በራሱ ባለሙያዎች በማዘጋጀት ቀላል ቀልጣፋና ዘመናዊ የአሰራር ሥርዓቶችን ለመከተል የሚያስችል ጅማሮዎችን እያስቀጠለ ነው፡፡ በሌላም በኩል የዓለም አቀፍ የአሰራር ደረጃዎችን ከማስረጽ አኳያም EOMS ISO- 21001/2018 የምዘና ሂደቱን በማጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡

ከስልጠና ፍላጎት አኳያ የአጫጭር ስልጠና ከመቼውም በላይ ትኩረት የተሰጠው ሲሆን በተለይ ወደ መካከለኛው ምስራቅ ለመሄዱ እህቶቻችን ስልጠና በመስጠትና COC (ሲኦሲ) ምዘና እንዲወስዱ በማድረግ ዜጎቻችን የተሻለ የሥራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

ነገር ግን በ1991ዓም ሞዴል የማሰልጠኛ ሆቴል እንዲሁም ለስልጠና ማስፋፊያ ቦታ አመቺነት በወቅቱ ካሉ የመንግስት ሆቴሎች የገነት ሆቴል የኢንስቲትዩቱ አካል ተደርጎ በአዋጅ ቢሰጠውም እስካሁን ባሉ ሂደቶች ወደ ኢንስቲትዩቱ ስሙ ባለመዞሩ ምክንያት የማስፋፊያ ግንባታ ማድረግ አለመቻሉ ለመደበኛ፣ አጫጭርና የተከታታይ ትምህርትን በሥፋት ለማካሄድ የስልጠና ቦታ ችግር ሆኖበታል፡፡

ዘርፉ በርካታ ባለሙያዎችን ያፈራ ለሀገራችን ብሎም ከምስራቅ አፍሪካ ጭምር ተወዳዳሪ ሲሆን የሚችል የሚሹ ጉዳዮችን እንደራዕዩ በስልጠና፣ በጥናትና ምርምር፣ በማማከር እንዲሁም በቴክኖሎጂ ሽግግር ከቀዳሚዎቹ አንዱ ለመሆን የሚያደርገውን ጥረት ወደተሻለ ደረጃ በማሳደግ መንግስትና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንደሚያበረክቱ ተስፋ እናደርጋለን፡፡

ጥራት ያለው _ ስልጠና ስለመስጠት

የተቋሙ አቅሙን በማሳደግ በሙያው መምህራን እንዲገነባ ከመደረጉም በላይ ቀጣይነት ባለው የከፍተኛት ምህርት ስልጠና መምህራን እውቀታቸውን እንዲያሳድጉም እየተደረገ ይገኛል፡፡ ተቋማችን በአሁኑ ጊዜ በስምንት የሙያ መስኮች ሥልጠና የሚሰጥ ሲሆን በሆቴል ቱሪዝም ዘርፍ በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የስልጠና መስኮች በአዲስ መልክ ተዘጋጅቷል፡፡

በዲግሪ፡- በሆቴል አስተዳደር
በቱሪዝም አስተዳደር

በደረጃ አራት

1. በእንግዳ አቀባበል
2. በቤት አያያዝ
3. በምግብና መጠጥ ቁጥጥር
4. በምግብና መጠጥ መስተንግዶ
5. በኬክ ዝግጅት
6. በቱሪስት አስጎብኝ

በደረጃ አምስት

7. በክሉናሪ አርት(በምግብ ዝግጅት )
8. በቱርኦፐሬሽን

በተቋማችን በሁለቱም የሙያ ዘርፎች እስካሁን 25ሺህ በላይ የመደበኛና ተከታታይ የተምህርት ክፍል የተመረቁ ሲሆን ሆኖም በየዓመቱ ከሚሰለጥኑ የሥራ ላይ ስልጠና የሚያገኙትን አያካትትም፡፡

የተግባር ትምህርትን በተመለከተ የሆቴል ሰልጣኞች በተግባር በተቋሙ ከሚያገኙት ሥልጠና ባሻገር በከተማው የሚገኙ ባለኮከብ ሆቴሎች የትብብር ስልጠና ያገኛሉ፡፡ የቱሪዝም ሰልጣኞች በቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎቻችን በሶስት አቅጣጫ ሙሉ መዳረሻዎቻችን ከመምህራን ጋር በመንብኘት የተግባር ሥልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም በአስጎብኝ ድርጅቶች አማካኝነት የትብብር ስልጠና ያገኛሉ፡፡

ተቋሙ በአሁኑ ጊዜ መንግስት ለዘርፉ የሰጠውን ልዩ ትኩረት መሰረት ያደረገ ስልጠና የሚሰጥባቸውን የሙያ መስኮች ደረጃ በማሳደግና በዘርፉ የልህቀት ማዕከል ለመሆን የሚያስችሉ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የዚህ እንቅስቃሴ አካል የሆነ የተቋሙን ስልጠና ደረጃ ዓለማቀፋዊ ተወዳዳሪ እንዲሆን የሚያስችል ISO 21001/2018 አንዱ ነው፡፡ ሌላው በቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ኢንደስትሪውን በጥናትና ምርምር መደገፍ የሚያስችሉ ሥራዎች ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ሲሆን ዘንድሮ በገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች ለሥራ ዕድል ፈጠራ ያላቸውን አስተዋጽኦ የዳሰሰ ጥናት መሰራቱ ነው፡፡

በዘርፉ ስልጠና የሚሰጡ የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆችን የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት እየተከናወኑ ካሉ ሥራዎቻችን በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

መንግስትም ተቋሙን በበጀት በመደገፍና ተጠሪነቱን ለሥራና ህህሎት ሚኒስቴር አድርጎ በአዲስ መልክ ሲያደራጀው ቱሪዝም ዘርፉን የሰለጠነ የሰው ኃይል ልማት ላይ በሰፊው እንዲሰራ ከማቀድ አንጻር መሆኑ ዕሙን ነው፡፡

ቱሪዝም ዘርፉ ሀገራችን ካላት የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ መስህብ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርስ አንጻር ምንም ያልተሰራበት በመሆኑ ዘርፉን መደገፍና በዘርፉ የሰለጠነና የበቃ የሰው ኃይል ማፍራት ልንመልሰው የሚገባን የወቅቱ ጥያቄ ነው፡፡

ስለሆነም ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በአሁኑ ጊዜ የመንግስት አስተዳደር ሪፎርም ሥርዐትን ተግባራዊ እያደረገ የሚገኝ ሲሆን ለ ሥራ አመቺ የሆኑ መመሪያዎችን እና የአሰራር ማዕቀፎችን በራሱ ባለሙያዎች በማዘጋጀት ቀላል ቀልጣፋና ዘመናዊ የአሰራር ሥርዓቶችን ለመከተል የሚያስችል ጅማሮዎችን እያስቀጠለ ነው፡፡ በሌላም በኩል የዓለም አቀፍ የአሰራር ደረጃዎን ከማስረጽ አኳያም EOMS ISO-21001/2018 የምዘና ሂደቱን በማጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡

ከስልጠና ፍላጎት አኳያ የአጫጭር ስልጠና ከመቼውም በላይ ትኩረት የተሰጠው ሲሆን በተለይ ወደ መካከለኛው ምስራቅ ለመሄዱ እህቶቻችን ስልጠና በመስጠትና ሲኦሲ ምዘና እንዲወስዱ በማድረግ ዜጎቻችን የተሻለ የሥራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የበኩላችንን እየተወጣን እንገኛለን፡፡

ነገር ግን ከመደበኛ አጫጭርና የተከታታይ ትምህርትን በሥፋት ለማካሄድ የስልጠና ቦታ ችግር ሆኖበታል፡፡ በ1991ዓም ሞዴል የማሰልጠኛ ሆቴል እንዲሁም ለስልጠና ማስፋፊያ ቦታ አመቺነት የገነት ሆቴል ታሳቢ ተደርጎ ቢሰጠውም እስካሁን ባሉ ሂደቶች ወደ ኢንስቲትዩቱ ስሙ ባለመዞሩ ምክንያት የማስፋፊያ ግንባታ ማድረግ አለመቻሉ፣ በ1961 በኢትዮጵያ እና በእስራኤል መንግስት ትብብር የተገነባው የኢንስቲትዩቱ ግቢ በኮሪደር ልማቱ አብዛኛው ቦታው ለመንገድ ማስፋፊያ ተወስዷል አሁን ባለው ሁኔታ ለስልጠና ምቹ ባልሆነ ሁኔታ ውስጥ ይገኛል፡፡

ዘርፉ በርካታ ባለሙያዎችን ያፈራ ለሀገራችን ብሎም ከምስራቅ አፍሪካ ጭምር ተወዳዳሪ ሊሆን የሚችል ተቋም በማሳደግ መንግስትና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡

## ነገ

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ትኩረት ሰጥተን ሰርተን እንደራዕዩ በሀገራችን ብቻ ሳይሆን ከአፍሪካ በቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ በስልጠና ፣ በጥናትና በምርምር እንዲሁም ዘርፉን በማማከር ከቀዳሚዎቹ አንዱ እንዲሆን ለመሥራት የማስፋፊያ ቦታው አስፈላጊነት ዛሬ ነገ የማይባል ነው፡፡

# EASTRIP

## በምርምር፣ በማማከር እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ዘርፍ

በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የምርምር፣ ማማከር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ይታሰብ ሱዩም ገለጻ ተቋሙ ከተሰጡት ተልዕኮች አንዱ ምርምርና ማማከር እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግር ማካሄድ ነው፡፡ እነዚህን ተልዕኮች በመደበኛና በ2016 በጀት አመት በተቋማችን መተግበር በጀመረው የምስራቅ አፍሪካ የክህሎት ትራንስፎርሜሽንና ቀጣናዊ ትስስር ፕሮጀክት (በEASTRIP) በተለያዩ ዘርፎች የገንዘብ ድጋፍ በማግኘት እየተከናወነ ይገኛል፡፡

በዋናነት ከEASTRIP ጋር በማስተሳሰር ከተሰሩ ተግባራት መካከል በምርምር ዘርፍ በተቋማችን በመደበኛውና በማታው ተከታታይ መርሃ ግብር የተመረቁ ተማሪዎች ምን ላይ ደረሱ የሚል ጥናት ሲሆን ስናጠና እናዚህ ተማሪዎች ስራ ላይ ናቸው ወይ አይደሉም በኢንዱስቱሪው ቀጥለዋል ወይስ አልቀጠሉም የሚሉት ስሆን በኢንዱስትሪው ተቀጥረው ከሆነ እርካታቸው ምን ይመስላል የሚል ና ኢንዱስትሪው እራሱ ምን ያህል በኛ ተማሪዎች በእውቀት በክህሎትና በአመለካከት የሚፈለገውን ያክል ረክቷዋል ወይ የሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ማግኘት የራሳችንን የማሰልጠን ዜዲያችንንና ካሪኩለም ጭምር እንዲንፈትሽና እንዲናይ ያደርገናል ብለዋል፡፡ ተቋሙ 55 ዓመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም በዚህ ርዕስ ምንም ጥናት አልተሰራም ነበር አሁን ግን ከ EASTRIP በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ወደ ኋላ 2012 ዓ ም ፤ 2013 ዓ.ም እና 2014 ዓ ም ድረስ ያሉትን አንድ ጊዜ አካተው እንደተሰራ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ይታሰብ ስዩም ይገልጻሉ፡፡

> የመጀመሪያው አጠቃላዩ ለአካባቢው ማህበረሰብ ፕሮጀክቶቹ ፀዘውት የመጡትን ቱርፋት ግንዘቤ እንዲፈጥሩ ማድረግ

ይህም ጥናታዊ ጽሁፍ የጥናት ተቋም እንደመሆኑ መጠን በውስጥ ባሉ አጥኚዎችና አሰልጣኞች እንደተሰራ ተገልጿል፡፡

የ2015 ዓ.ም ተመራቂዎች ደግሞ ለመስራት ቡድን በማዋቀር ዝግጅቱን አጠናቋል ፤ እነዚህ ሥራዎች የመጀመሪው ሥራ ሲሆን ሁለተኛው የገበያ ፍላጎት መሰረት ያደረገ ሥራ ከዚህ በፊት እ ኤ አ 2016 እና 2018 መጠነኛ ጥናቶች በተቋም አቅም ተሰርቷል፡ በኢንዱስትሪው ያለውን የሰለጠነ የሰው ሀይል ለማወቅም ይረዳል፣ ከዚህ በፊት የኢንድስሪውን ፍላጎት መሰረት አድርገን ነው፤ ዘንድሮ ግን አቅርቦት ጨምርን በመስራት ፍላጎትና አቅርቦትን ለማጣጣም በእኛ ተቋም ቢቻ ሳይሆን በሌሎች ከ20 በላይ ዩንቨረስቲዎች ያለውን አቅርቦት በመለየትና ከሆቴሎች ፍላጎት ጋር እንዴት ማጣጣም ይቻላል የሚለውን ትልቅ ሀገራዊ ጥናት እየተጠና መሆኑን በመግለጽ ይህም የገንዘብ ድጋፍ ያገኘው በ EASTRIP ፕሮጀክት እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ሶስተኛው ሥራ የስልጠና ፕሮግራሞችን ለማስፋት ማለትም በእኛ እስከ ስምንት ሙያ ደረጃዎች ስልጠና እየተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሆቴል ዘርፎች በአምስት በምግብ ዝግጅት፣ በምግብና መጠጥ መስተንግዶ፣ በምግብና መጠጥ ቁጥጥር፣ በቤት አያያዝና ላውንዴሪ እንዲሁም በእንግዳ አቀባበል ሲሆን በቱሪዝም ዘረፍ ሶስት ሙያ ደረጃዎ በቱር ኦፕሬሽን፣ ቱር ጋይድ እና ማርኬትን ስልጠናዎች እየተሰጡ ይገኛሉ፡፡

ይህንን ለማስፋት ሁለት መሰረታዊ ጥያቀዎች በመጠየቅ እነዚህ ሙያ ደረጃዎች አብዛኛው በደረጃ አራት ሲሆን ሁለት ሞያዎች በደረጃ አምስት እየተሰጠ ስለሆነ ደረጃቸውንና በኢንዱስቲሪው ተፈላጊነት አኳያ የሚለው አንዱን ጥያቄ ሲሆን ሁለተኛው ከዚህ ውጭ ተጨማሪ ኢንዱስቲሪው የሚፈልጓቸው ሞያዎች ካሉ ብለን ጠይቀን በዚህ መሰረት አዳዲስ የሙያ አይነቶችን እንዲናገኝ ረድቶናል፡፡ ለምሳሌ ባር ቴንደር፣ ባሪስታ

ዊልነስ ሰርቨስ የመሳሰሉትን ሙያዎች በጥናት ተገኝቶ ስልጠናዎች ቢያንስ በአጫጭር ስልጠናም ቢሆን እንዲሰጡ አቅጣጫ ተሰጥቷል፤ እነዚህንም የምርምር ስራዎች በEASTRIP ፕሮጀክት ድጋፍ መሰራታቸውን አቶ ይታሰብ ገልጸዋል፡፡

ሌላው በEASTRIP ፕሮጀክት ከሚሰሩ ሥራዎች አንዱ ሀገር በቀል ዕውቀት ላይ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ገበታ ለሀገር ሶስቱም ፕሮጀክቶች ላይ ጥናት ተካሂዷል፡፡ በነዚህ ፕሮጀክቶች ምንምን ሥራ ዕድሎች ሊፈጠ ሩ ይችላሉ፣ በተፈጠሩ መስኮች ላይ ስልጠናዎችን መስጠት ሲሆን የዚህ ጥናት ውጤት ሁለት አይነት ስልጠናዎች እንዲንሰጥ አድርጎናል፡፡

የመጀመሪያው አጠቃላይ ለአከባቢው ማህበረሰብ ፕሮጀክቶቹ ይዘውት የመጡትን ቱርፋት ግንዛቤ እንዲፈጥሩ ማድረግ፤ በፕሮጀክቱ ምክንያት የሚፈርስ የሚፈናቀል የሚለውን የተሳሳተ አመለካከት ትቶ ይዘውት የመጡትን ድል ለማህበረሰቡ በወረዳ በቀበሌ ደረጃ ማሳወቅ አንዱ ስሆን ሁለተኛው በተመረጡ መስኮች የአከባቢውን ወጣቶች በትምህርታቸው እስከ መጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው መኖራቸው በሶስቱም ቦታ ስለተረጋገጠ እነሱንም ምንም ስልጠና ያላገኙትን የመለየት ሥራ ተሰርቷል፡፡

ይህንን መሰረት በማድረግ በኮይሻ ስልጠና ተሰጥቷል
፤ በቀጣይ በወንጪ ና በጎርጎራም የሚሰጥ ይሆናል፡፡ ከዚህ ጋር አብሮ እየሄደ ያለው ባህላዊ ምግብ ዝግጅት እንደ ተቋም ከዚህ በፊትም አቅደን እየሰራን ያለንበት ቢሆንም በዚህ ዓመት ከፕሮጀክቱ ጋር ለማስተሳሰር ጥረት መደረጉን ጠቁመው ዘንድሮ የስልጤ፣ ሀዲያና ወላይታ ባህላዊ ምግቦች ጥናት መደረጉን ምክትል ዋና ዳሬክተሩ ገልጸ ዋል፡፡ ከዚህ በፊት የተሰሩ አምስት ክልል ባህላዊ ምግቦችን ወደ ሰነ በህትመት ፕሮጀክቱ ያግዘናል ብለ ያሉት አቶ ይታሰብ እዚህ የተሰሩ ባህ ከሁለት ትላልቅ ሆቴሎች ጋር ተነጋገ ፌስቲቨል ለማዘጋጀት ሰነዶችም




ማድረግና ሆቴሎችም በምግብ መዘርዝራቸው ውስጥ እንዲያካቱ የማድረግ ሥራዎች ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ባህላዊ ምግቦች ተጠንተው ፣ ተሰንደው ወደ ኢንዱስትሪው እንዲገቡ ብቻ ሳይሆን ከዚህም ሚናቸው ከፍእንዲል ስለሚፈለግ ባህላዊ ምግቦች ለሥራ ዕድልና ምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አኳያ ያለው ፋይደ ምን ይመስላል የሚል ጥናትም እንደተጀመረ ተገልጸዋል፡፡

በመጨረሻም ከEASTRIP ፕሮጀክት ጋር ለመስራት ከታቀዱት ሥራዎች አንዱ የቱሪዝምና ሆቴል ዘርፍ መዝገበ ቃላት ለማዘጋጀት ታቅዷል፡፡ የሆቴልና የቱሪዝም ቃላት አብዛኛውን ጊዜ እንግሊዝኛና ፈረንሳይኛ እየሆነ ለሥራ ስለተቸገርን ይህንን ለመፍታት ቡድን ተዋቅሮ ወደ ሥራ እንደተገባና በቀጣይ በሀገራችን በተለያዩ ቋንቋዎች እንደምተረጎምና ስለቱሪዝም ህብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ይሰራል ተብሏል፡፡

ከመደበኛው በጀት በተጨማሪ EASTRIP ፕሮጀክት በተቋሙ መተግበሩ ሥራዎች ያለበጀት እጥረት እንዲቀላጠፍና ያለንን የምርምር አቅም እንዲንጠቀም አስችሎናል ብለዋል፡፡

# ብሩህ አዕምሮዎች በክህሎት የበቁ ዜጎች

# Bright Minds; Skillful Citizens!

## 4 ^ኛው^ ሀገር አቀፍ የክህሎት ውድድርና 12^ኛው^ የቱሪዝምና እንግዳ ተቀባይነት ሳምንት

## 4th National Skills Competition and 12th Tourism & Hospitality Week



ሚያዚያ 2017 ዓ.ም

TOURISM
TRAINING INSTITUTE

# 2025

ለላቀ ብቃት እንተጋለን!

*We Strive for Excellence*

Address:-
Tourism Training Institute (TTI)
+251 115 30 81 75
info@tti.edu.et
tti (Tourism Training Institute)
tti (Tourism Training Institute)
www.tti.edu.et
4350 (Addis Ababa, Ethiopia)